ክብርት ወ/ሮ ወርቅሰሙ ማሞ!

የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት ዋና አፈ-ጉባኤ!

የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት!

ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች!

ክቡራትና ክቡራን!

1. በአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግስት አንቀፅ 116(2) እና የዋና ኦዲተር መ/ቤት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 186/2003 አንቀፅ 6 እና አንቀፅ 10(2) ለመ/ቤቱ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የተከናወኑ ተግባራትን የሚገልፅ ሪፖርት ዋና ኦዲተሩ ለተከበረው ም/ቤት እንደሚያቀርብ የተደነገገ በመሆኑ ይህን ሪፖርት አቀርባለሁ፡
2. በዚህ ሪፖርት የመ/ቤታችን የ2011 በጀት ዓመት የ11 ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በአጭሩ፣ መ/ቤታችን ያከናወነው የ2009 በጀት ዓመት የክልሉ የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ እንዲሁም የ295 መ/ቤቶች የ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ የፋይናንስና ሕጋዊነት እና የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤት የክትትል ኦዲት ሪፖርት በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

## የ2011 በጀት ዓመት የ11 ወራት የዕቅድ አፈፃፀም፤

## የኦዲት ልማት ሰራዊት ግንባታ አፈፃፀም

3. በ5ቱ የአቅም ግንባታ ስትራቴጅዎች በአመለካከት፣በክህሎት፣በአሰራር፣ በአደረጃጀትና በግብዓት የማብቃትና የልማት አቅሞችን ወደ ተቀራረበ የመፈፀም አቅም የማብቃት ጉዳይ ነው፡፡ ከኦዲት ልማት ሰራዊት ግንባታ አንፃር በ2011 በጀት ዓመት የአቅም ግንባታ ስትራቴጅዎችን በተደራጀ መንገድና በለውጥ ፕሮግራሞች አግባብ በመፈፀም የተሻለ የኦዲት ልማት ሰራዊት ለመገንባት ዕቅድ በመያዝ የመ/ቤታችን ፈፃሚዎች በ4 የልማት ቡድኖችና በ72 የ1ለ5 አደረጃጀቶች ተደራጅቶ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ አደረጃጀቶች በየቀኑ የመረጃ ልውውጥ እና ሳምንታዊ የስራ ላይ ግምገማ በማድረግ፣በየ2 ሳምንቱ በተመረጠ ርዕሰ-ጉዳይ የመማማርና ወደ ተቀራረበ ብቃት ለማምጣትና የመረጃ ፍሰት መፍጠር በቃለ-ጉባዔ የተደገፈ ውይይት በማካሄድ፣ በተቻለ መጠን በየደረጃው ግብረ-መልስ እየተሰጠ ለመምራት ጥረት ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በፈጻሚዎች መካከል የተቀራረበና የተለወጠ አመለካከት ለማምጣት የተለያዩ መድረኮችን በመፍጠር የጋራ ውይይቶች ተካሂደዋል፡፡ በዚህ ደረጃም በልማት ቡድንና በመ/ቤት ደረጃ የተካሄዱ መድረኮች፣ የተደረጉ የስራ ውጤት ግምገማዎችና ውይይቶች ግልጽነትና የአመለካከት መቀራረብ በመፍጠር የተገኙ ግብዓቶችና ክህሎቶችም ለእቅዶቻችን ማሳካት አግዘውናል፡፡
4. ከመልካም አስተዳደር ስራዎች አንፃር በ2011 በጀት ዓመት ዕቅዳችን አስቀድመው የተለዩ ተግባራትን ለማከናዎን ማለትም የሪፎርም ስራዎችን አፈፃፀም አጠናክሮ ከማስቀጠል አጠቃላይ ዕይታ በመነሳት ከዚህ በፊት የኦዲት ሽፋን ያላገኙ ወረዳዎች የኦዲት ሽፋን እንዲያገኙ መደረጉ፣ የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲቱ ወቅታዊ መሆኑ፣ የክልሉ መንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የውሃ አገልግሎት ጽ/ቤቶችና

ማዘጋጃ ቤቶች ሂሳባቸውን እየዘጉ በተፈቀደላቸው የግል ኦዲተሮች ኦዲት እንዲያስደርጉ በተደጋጋሚ በደብዳቤ በማሳወቅ ትኩረት መሰጠቱና በስልጠናም መታገዛቸው፣ ዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈፀሚያ (SDG Budget) ቅድሚያ ተሰጥቶ ኦዲት እንዲደረግ ልዩ ክትትል መደረጉ፤ የህዝብ ከፍተኛ ጥቅም ያለባቸውን የክልሉ 10 የከተሞች መሰረተ-ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም (ULGDP) እና አዲሶች 22 የከተሞች ተቋማዊና መሰረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም (UIIDP)ተጠቃሚ ከተሞችን ለይቶ ቅድሚያ የኦዲት ሽፋን እንዲያገኙ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በመከታተል፣ ከህዝብና ከወኪሎቻቸው የሚቀርቡ የልዩ ኦዲት ስራ ጥያቄዎችና ለፍትሃዊ ውሳኔ እንዲግኝ በፍርድ ቤት የሚታዘዙ የኦዲት ስራዎችን ምላሽ ለመስጠት እንዲያስችለን ለልዩ ኦዲት ስራ አመራር መከታተያ መመሪያ በማሻሻልና ስራውን በልዩ ትኩረት በመፈጸም፤ በስራ ላይ ለሚነሱ የኦዲት ስራዎች ቅሬታ የአፈታትና ቅሬታዎችን ፈጥኖ ምላሽ መስጠት የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት የተሰሩ ስራዎች በአበረታችነት የታዩ ናቸው፡፡

5. የውስጥና የውጭ ደንበኞች አገልግሎት አሰጣጣችን በዓመቱ 94% የደንበኛ እርካታ ለመድረስ በዕቅድ የተያዘ ሲሆን በየ11 ወሩ መረጃ በመሰብሰብ ከደንበኞች በአማካኝ 89% እርካታ እንዳለ በዳሰሳ ጥናት የተለየ ሲሆን ይህም በዓመቱ በዕቅድ ከተያዘው አኳያ ሲታይ የዕቅድ አፈፃፀሙ 94% ነው፡፡ የአገልግሎት አሰጣጥ እርካታ መጠይቅ በማዘጋጀትና በኦዲት መውጫ ስብሰባ ወቅት ኦዲት አስደራጊዎች በጽሁፍ በሚሰጧቸው አስተያየቶች መሰረት በጥንካሬ የተገለጹትንና የሚስተዋሉ ክፍተቶችን በመለየት እየተገመገመ ግብዓት እንዲሆን ከመደረጉም በላይ ለሚዛናዊ ውሳኔና ለግልጽነትና ተጠያቂነት መጠናከር እያገዘ መሆኑን፣ የኦዲት ስራው በየ6 ወሩ ተከፋፍሎ (በኢንትሪም ኦዲት ስልት) መሰራቱ ስህተቶችን በወቅቱ ለማስተካከል ስለሚረዳ በዚሁ እንዲቀጥል የሚሉ ገንቢ አስተያየቶች ናቸው፡፡ በውስንነት ደንበኞች የሰጧቸው አስተያየቶች ሲታዩ በየአመቱ የኦዲት አገልግሎት የማያገኙ ተቋማት መኖር የሚለው የሚጠቀስ ነው፡፡

6. የውጤት ተኮር ሥርዓት(BSC) ከሪፎርም ፕሮግራሞች መካከል ትኩረት ተሰጥቶት በመተግበር ላይ ከመሆኑም ባሻገር አጠቃላይ ውጤቱም ከሌሎች የሪፎርም ስራዎች ጋር ተዳምሮ የመፈጸም አቅሙ የተሻለና መልካም አስተዳደርን ያሰፈነ ተቋማዊ ሁኔታን ማረጋገጥ የሚጠይቅ ነው፡፡በተለይም ኦዲት በአጠቃላይ የመንግስት አሰራር ግልፀኝነትን የተላበሰና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን የሚያበረክተው አስተዋፅኦ የጎላ በመሆኑ በዚሁ አግባብ መታየት ይኖርበታል፡፡

በ2011 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ውጤት ተኮር ምዘና መሰረትም መመዘን ከሚገባቸው 308 (ሴት-80) ሰራተኞች መካከል 276 (ሴት-68) ሰራተኞች በምዘናው አልፈዋል፡፡ በምዘናው ካለፉ ሰራተኞች መካከል 93 (ሴት -17) ሰራተኞች (ከአጠቃላይ ተመዛኞች 33.65%) ከፍተኛ ያገኙ ሲሆን ቀሪዎቹ 183 (ሴት-51) ሰራተኞች (ከአጠቃላይ ተመዛኞች 66.30%) መካከለኛ ያገኙ ናቸው፡፡ ከውጤት ተኮር ስርዓት ጋር በተያያዘ ያሉብን ውስንነቶች ተከትሎ ለ2ኛው ግማሽ ዓመት ውጤት ተኮር ስርዓት ከችግሮች በሚያወጣ መንገድ ውል ተይዞ እየተሰራ ይገኛል፡፡

7. **የኦዲት ኮሚዩኒኬሽን ስራዎች አፈፃፀም፤**

የኦዲት ኮሚዩኒኬሽን ስራችን በዋናነት የፋይናንስ ግልፀኝነትንና ተጠያቂነትን ለማስፈን በሚያስችሉ እንቅስቃሴዎች ላይ ትኩረቱን አድርጎ በሐገራዊ፣ ክልላዊና ወቅታዊ ጉዳዮች ለመ/ቤቱ ማህበረሰብ ግንዛቤ መፍጠርና የተቀራረበ የአመለካከት አንድነት መፍጠርን ታሳቢ አድርጎ የሚሰራ ስራ ነው፡፡ከዚህ አንጻርም የክልላችን ሚዲያ ለመጠቀም የሚያስችል ፕሮግራም ተግባራዊ ማድረግና የሙያና የመ/ቤቱ ተልዕኮ የተመለከተ የህትመት ስራዎችን ማሳተምና ተደራሽ ማድረግ የዕቅዳችን አካል በማድረግ ስለአገራዊ፣ ክልላዊና ስለወቅታዊ ኩነቶች ትኩረት ሰጥቶ ግንዛቤ የመፍጠር ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ከኦዲት ኮሙኒኬሽን የትኩረት ነጥብ አንፃር የመድረክ ዝግጅት በተመለከተ በዚህ 11 ወር ውስጥ በአጠቃላይ 30 ልዩ ልዩ መድረኮች የተካሔዱ ሲሆን 18ቱ አገራዊና ክልላዊ ከነቶች 12ቱ የኦዲት ፅንሰ ሃሳብና ግንዛቤ ለማስጨበጥ ለመ/ቤቱ ስራተኞች፣ ህዝብ ክንፎች ወይም አጋር አካላት የተዘጋጁ ስልጠና ናቸው፡፡ ለአብነት በጥቂቱ የመ/ቤቱ የ2010 ዓ.ም ዕቅድ ክንውን ግምገማና የ2011 በጀት ዓመት ዕቅድ ትውውቅ፣ በክልሉ እስከ ወረዳ ለተዋቀረው የኦዲት ግኝት አስመላሽ ግብረ ሃይል ኮሚቴ የጋራ መድረክ ና የሠራተኞች ሂስ-ግለ ሂስ መድረኮች ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## የኦዲት ሥራ ዕቅድ አፈፃፀም፣

### የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት አፈፃፀም፣

8. በ2011 በጀት ዓመት በፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ለማከናወን ከታቀደው 332 መ/ቤቶች አንጻር በ11 ወሩ 330 መ/ቤቶችን በማከናወናችን የኦዲት ሽፋን አፈጻጸሙ ሲታይ የዕቅዳችንን 99.6% መፈጸም ተችሏል፡፡

በ2011 በጀት ዓመት በፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት በስትራቴጅያዊ ዕቅድ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ኦዲት ተደራጊዎች ቁጥር ሽፋን አንፃር ሲታይ በአመቱ 75% ለማድረስ ታቅዶ በ11 ወሩ 330 መ/ቤቶችን ማከናወናችን ከዓመቱ የኦዲት ሽፋናችን 74.6% መድረስ ተችሏል፡፡

ሽፋን ከበጀት አንፃር እስከ 80% የወጪ በጀት እና እስከ 45% የገቢ በጀት ሽፋን ለማድረስ ታቅዶ ለክልሉ የ2010 በጀት ዓመት የተፈቀደውን አጠቃላይ በጀት ብር 37.6 ቢሊዮን መነሻ በመያዝ በኦዲት የተሸፈኑ መ/ቤቶች አጠቃላይ በጀት ብር 23.2 ቢሊዮን የኦዲት ሽፋን ያገኘ በመሆኑ አፈፃፀሙ 62% ላይ ይገኛል፡፡ የገቢ ኦዲት ሽፋንን በሚመለከት ክልሉ በራሱ አቅም ለመሰብሰብ ከያዘው ዓመታዊ የገቢ መጠን ብር 10.5 ቢሊዮን ላይ ኦዲት የተደረጉ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች ሽፋን የተሰጠው ለብር 5.2 ቢሊዮን በመሆኑ ሽፋኑ 50%ነው፡፡ ይህ ከዕቅድ አንጻር የወጪ በጀት ዝቅ ያለበትና የገቢ በጀት ኦዲት ሽፋን ከፍ ያለበት ምክንያት ከፍተኛ ገቢ ሰብሳቢ የሆኑ በርካታ ተቋማትን ቅድሚያ ተሰጥቶ ኦዲት በመደረጋቸው ነው፡፡

### የክልሉ የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ ኦዲት በተመለከተ፣

9. መ/ቤታችን በየዓመቱ ተዘግቶ የሚቀርብለትን የክልሉን የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ ኦዲት እያደረገ አስተያየት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም መሠረት የ2009 በጀት ዓመት የክልሉ የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ ኦዲት ተጠናቀ ‹‹ከዚህ በስተቀር›› የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በግኝቶቹ ላይም የማስተካከያ እርምጃ እየወሰደ መሆኑን የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ት/ቢሮ በግብረ መልሱ አሳውቋል፡፡ዋና

ዋና ግኝቶችም በዚህ ሪፖርት ቀርበዋል፡፡ በሌላ በኩል የ2010 በጀት ዓመት የክልሉ የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ ምርመራ ተጠናቆ የመውጫ ስብሰባ አጀንዳና ረቂቅ ሪፖርት ዝግጅት ላይ ሲሆን ውይይቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ሪፖረቱን ለማውጣት በ95% አፈጻጸም ላይ ይገኛል፡፡

## የክዋኔና አካባቢ ጥበቃ ኦዲት አፈፃፀም፤

10. ከክዋኔ ኦዲት አንፃር በ11 ወራት መ/ቤቱ በክዋኔ ኦዲት የ7.6 መ/ቤቶችን ኦዲት ለማድረግ እቅድ ተይዞ በአንፃራዊ ስሌት የ6.9 መ/ቤቶችን ኦዲት በማድረግ የእቅዱን 90.7% ለማከናወን ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ከሰኔ 30/2010 ዓ.ም በፊት የተጀመሩትን ጨምሮ የ4 መደበኛ ክዋኔ እና የ5 የክትትል ስራዎች ሪፖርታቸው ወጪ የተደረገ ሲሆን የሌሎች የ9 መደበኛ የክዋኔ ኦዲቶች ከ84-100% የአፈፃፀም ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡

## የኦዲት ስልጠና፤ክትትልና የሙያ ብቃት ፈቃድ አሰጣጥ አፈፃፀም፤

11. መ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 186/2003 አንቀፅ 6 (2) (ሀ) መሰረት የመንግስት መ/ቤቶችንና የልማት ድርጅቶችን በራሱ ወይም በውክልና ኦዲት እንደሚያስደርግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሂሳባቸውን በግል ኦዲተሮች ኦዲት ላስደረጉና በማስደረግ ላይ ለሚገኙ የክልሉ መንግስት የልማት ተቋማት፤ የየከተሞች የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤቶችና በማዘጋጃ ቤት ደረጃ ለሚገኙ ከተሞች በቁጥር 16 በሚሆኑት ላይ የክትትልና ድጋፍ ስራ ተሰርቷል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ለግል ሒሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ፈቃድ መስጠትና የስራ ክትትል ተግባርን በተመለከተ በ11 ወሩ ለ7 የሂሳብ ድርጅት ፍቃድ፣ ለ15 (ሴት-2) የሂሳብ የግል ብቃት ማረጋገጫ፣ ለ2 የኦዲተር ድርጅት ፍቃድ፣ ለ15 (ሴት-2) የኦዲተር የግል ሙያ ብቃት ማረጋገጫ እና ለ2 በማህበር ለተደራጁ ኦዲት ድርጅት ፍቃድ በመመሪያው መሰረት ወደ ግል ስራ እንዲሰማሩ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ወስደዋል፡፡

ስልጠናን በሚመለከት የመ/ቤታችን ኦዲተሮች በቅድመ ስራና በስራ ላይ ሠልጣኝነት ደረጃ ተለይተው ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የአቅም ግንባታ ስራ ተካሂዷል፡፡ ከዚህም መካከል፤ ለጀማሪ ኦዲተሮች በመንግስት ሂሳብ አያያዝ ስርዓት፣ስለኦዲት ሙያና ስነ-ምግባር እና በመንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በስራ ላይ ላሉ የክዋኔ፣የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ማናጀሮችና ፈጻሚ ኦዲተሮች በግንባታ ሂሳብ አዋጅ.ደንብ፣ መመሪያ፤ በ2013 የሬጉላሪቲ የኦዲት ሙያ ማንዋል ዙሪያ ላይ የግንዛቤና ሙያዊ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

እነዚህ ሁሉ የአቅም ግንባታ ስራዎች ባለሙያዎች የኦዲት አሠራርና የስነ-ምግባር ደረጃዎችን ጠብቀው ኦዲቱን እንዲሰሩና ውጤታማነታቸው እንዲያድግ ብሎም ክህሎታቸውን ለአዳዲስ ባለሙያዎች በማስተላልፍ የሙያ አገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ ያደርጋል፡፡

## የኦዲት ግኝት ለማስመለስ የተደረገ ጥረት

12. ጠንካራ አፈጻጸሞችን ይበልጥ ለማጎልበትና ውስንነቶችን ለማረም ከ2004 በጀት ዓመት ጀምሮ የኦዲት ግኝቶች እርምጃ አወሳሰድ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ ወደ ስራ ገብቷል፡፡ የኦዲት ግኝት እርምጃ አወሳሰድ

ግብረ ኃይል በአጠቃላይ የፋይናንስ ግልፀኝነት እና አስተዳደር ሥርዓቱ ላይ የአቅም ግንባታ፣ ግንዛቤ የመፍጠርና የተጠያቂነት ሥርዓትን የማስፈን ተግባር ለተከታታይ ዓመታት ተከናውኗል፡፡በመሆኑም በእነዚህ የኦዲት ግኝቶች ላይ የተጠናከረ እርምጃ መውሰድ እንዲቻል በ2011 በጀት ዓመት ግብረ-ኃይሉ የማስፈጸሚያ ዕቅድ በማዘጋጀትና ከ5 ተቋማት የተውጣጣ የቴክኒክ ኮሚቴ በማቋቋም ወደ ስራ ገብቷል፡፡ ግብረ ኃይሉን በሁሉም ዞኖቹ በመስክ ተገኝቶ መረጃ የማጥራት፣ድጋፍና ክትትል ከማድረጉም በተጨማሪ ከክልሉ አብይ ግብረ-ሃይል ጋር በመሆን በየደረጃው ለተቋቋመው የኦዲት ግኝት እርምጃ አወሳሰድ ግብረ-ሃይል ግምገማዊ ስልጠና በመስጠትና በስልጠናው ለተነሱ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ሙያዊ ማብራሪያና ግንዛቤ መስጠት ተችሎል፡፡

በክልል ደረጃ አብይ እና የቴክኒክ ኮሚቴው በጋራ ተወያይቶ በናሙና በተመረጡ የክልል ቢሮዎች፣ ዞኖች እና ወረዳዎች በየጊዜው በውስጥም ይሁን በውጪ የሚገኙ የኦዲት ግኝቶች ሙሉ በሙሉ ለማስመለስ /እርምጃ ለመውሰድ/ያጋጠሙ ተግዳሮቶች (ችግሮች) ምን እንደሆኑ ኮሚቴው በመስክ በመገኘት በናሙና የተመረጡ 7 የክልል ተቋማት በማካሄድ የተገኙትን ግኝቶች በክልል ደረጃ በተዘጋጀው የኦዲት ግኝት አመላለስ መድረክ በስፋት በመወያየት አቅጣጫ ተሰጥቷል፡፡

### የሰው ሃይል መዋቅርና የስምሪት መረጃ፤

13. መ/ቤቱ የደሴ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሠራተኞች እና 4 ጊዜያዊ መደብ ጨምሮ 344 የሰው ኃይል የሚይዝ ድርጅታዊ መዋቅር ያለው ሲሆን አሁን ላይ ያለው የሰው ኃይል 324 ነው፡፡ ይህም የመዋቅሩን 94.18% ይሸፍናል፡፡ከዚህ ውስጥ 233/71.9%/አላማ ፈፃሚ እና 91/28.08%/ የአስተዳደር ሠራተኞች ናቸው፡፡ በመ/ቤቱ በስራ ላይ ካሉት 324 ሠራተኞች መካከል 238/73.4%/ ወንዶች፣ 86/26.5%/ ሴቶች ናቸው፡፡ ከዓላማ ፈፃሚዎች መካከል 3 ወንድ 1 ሴት ተሿሚ ይገኛሉ፡፡ ከኃላፊነት አንፃር የሴቶች ተሳትፎ ሲታይ 3 ሴት የዳሬክቶሬት ደረጃ ፣2 በቡደን መሪ (ማናጀር) ደረጃና 3 ኬዝ ቲም አስተባባሪ በአጠቃላይ 8 ሴቶች በሃላፊነት ደረጃ ተመድበው እየሰሩ ናቸው፡፡ በመ/ቤቱ በስራ ላይ ከሚገኙ ሠራተኞች መካከል 259 (79.9%) የመጀመሪያ ድግሪና ከዚያ በላይ ያላቸው ሲሆኑ ከዚህ ውስጥ የሴቶች 55(21.4%) ይሸፍናሉ፡፡ ከእድሜ አንጻር ሲታይ 141 (43.4%) በወጣት ዕድሜ ክልል የሚገኙ ናቸው፡፡

ከረጅም ጊዜ ሥልጠና አኳያ በ2ኛ ዲግሪ በትምህረት ላይ የሚገኙ ወንድ 24 ሴት 9 በድምሩ 33 ሲሆኑ ከዚህ በተጨማሪ በመጀመሪያ ዲግሪ ወንድ 1 ሴት 9 በድምሩ 10 ሰራተኞች በአጠቃላይ በትምህርት ላይ ካሉት መካከል 19 (44%) ሴቶች ናቸው፡፡

### የበጀት አፈፃፀምና አጠቃቀም፤

14. በ2011 በጀት ዓመት በም/ቤቱ የፀደቀና የተፈቀደው የመደበኛ በጀት ብር 40,832,728.00፤ ለካፒታል በጀት ደግሞ ብር 1,607,219.00 በድምሩ ብር 42,439,947.00 ፀድቆ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡የመደበኛ በጀት ድልድሉም ለደመወዝ ብር 22,604,658.00፤ለስራ ማስኬጃ ብር 18,228,070.00 የተመደበ ነው፡፡ በተጨማሪም በ11 ወሩ ከልማት አጋሮቻችን የተለያዩ ምንጮች በጀት ተመድቦአል፡

የ11 ወሩ በጀት አጠቃቀም ሲታይ ከመደበኛ በጀት ለደመወዝ ብር 20,420,936.00 (90.4%)፤ ለስራ

ማስኬጃ ብር 15,471,222.00 (84.8%) በድምሩ ብር 35,892,158.00 (ከመደበኛ በጀቱ 87.9%) ነው፡፡ የስራ ማስኬጃ በጀት የቀነሰበት ምክንያት አንዳንድ ዕቃዎች በመቅረብ ላይ በመሆናቸው ገና ወጪው ባለመጽደቁ ነው፡፡

የካፒታል በጀቱ አጠቃቀም ሲታይ ከፍተኛውን ድርሻ (ከ1.3 ሚሊዮን በላይ) የያዘው የአየር ማቀዝቀዣ (AC) መግጠም ሲሆን ይህን ማሽን ከማቅረብ ጋር በተያያዘ በሂደት ላይ ስለሆነ በቀጣይ ማሽኑ ሲገጠም ክፍያ የሚፈጸም ይሆናል፡፡በሌላ በኩል ከመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ ፕሮግራም (PBS-III) ከተመደበልን በጀት 100% እና ከከተሞች መሠረተ ልማት ድጋፍ ፕሮግራም (ULGDP-II) ከተመደበልን በጀት ላይም 88.8% ስራ ላይ ውሏል፡፡

በዚህ የበጀት አፈጻጸም ወቅት የተመደበውን በጀት በፋይናንስ አሰራር እና በተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት መሠረት ለመምራት ጥረት የተደረገ ሲሆን በውስጥ ኦዲተሮቻችን አማካኝነት እየተመረመረና ለሪፖርቱ ግብረ-መልስ እየተሰጠ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ጭምር የተላከ ሲሆን የተስተዋሉ የክፍያ፣ የምዝገባና ተያያዥ ግኝቶች ላይ ከስር ከስሩ የማሻሻያ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡የግዥ አፈጻጸሙን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ በተያዘው የግዥ እቅድ መሠረት አብዛኛውን ግዥ በግልጽ ጨረታ ዘዴ ለማከናወን ተችሏል፡፡ የመ/ቤቱ የንብረት አያያዝ በመመሪያው መሠረት በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውል እየተደረገ ሲሆን ለኦዲት ምቹ፣

ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው ሆኖ እንዲተገበር እየተደረገ ይገኛል፡፡

**የሴክተር ዘለል ተግባራት አፈፃፀም፤**

**የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከል ስራዎች፤**

15. የመ/ቤቱ ሠራተኞች ከየወሩ ደመወዛቸው እያዋጡ በሚያጠራቅሙት የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያ ፈንድ ማህበር ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸው ባልደረቦችና ማህበሩ ለሚያሳድጋቸው 4 ህጻናት ወርሃዊ ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል፡፡

የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያ ተግባራትን አካቶ መስራት(ሜይንስትሪሚንግ) ዕቅድ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው የተላከ ሲሆን በቢሮ ውስጥ ሠራተኞች ስለቅድመ ጥንቃቄ፣ ስለቫይረሱ ባህሪ የመተላለፊያና መከላከያ ዘዴዎቹ ወዘተ ውይይት እየተደረገና ስለአፈጻጸሙም በየሩብ ዓመት ሪፖርት እየተዘጋጀ ለሚመለከተው በመተላለፍ ላይ ይገኛል፡፡

**ስርዓተ ፆታን አካቶ የመስራት እንቅስቃሴ፤**

16. ስለስርዓተ ጾታ ተገቢውን ግንዛቤ በመያዝ በሁሉም ስራ አካቶ በመስራትና ሪፖርቶችም በጾታ ተተንትነው የሚቀርቡበት ስርዓት ተዘርግቶ እየተፈጸመ ሲሆን በሴቶች ልዩ ማበረታቻ መመሪያ መሰረት በ11 ወሩ ከተፈፀመው 23 የቅጥር ስምሪት ላይ 7 ሴቶች በልዩ ማበረታቻው መሰረት የተቀጠሩ ናቸው፡፡

**ክብርት አፈ-ጉባዔ!**

**የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

ቀጥሎ የ2009 በጀት ዓመት የክልሉ የተጠቃለለ ፈንድ (የትሬዠሪ) ሂሣብ ኦዲት ውጤት ዋና ዋና ግኝቶችን አቀርባለሁ፤

**በክልሉ በተሰብሳቢ የተያዘ ሂሳብ፤**

17. በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሪፖርት የተመለከተው የክልሉ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 9,886,796,071.97 በወቅቱ ሳይሰበሰብ /ሳይወራረድ/ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ተሰብሳቢ ላይም 43.45% የሚሆነው በባለበጀት መ/ቤት ውስጥ ሌሎች (ከአንዱ ለሌላው የተሰጠ)፣ 21.37% ለስራ ተቋራጮች ቅድሚያ ክፍያ፣ 18.68% ለእቃ አቅራቢዎችና ለግዥ ሠራተኞች ቅድሚያ ክፍያና ለህብረት ስራ ማህበራት ብድር የተሰጠው በድምሩ 83.5% የሆነውን ተሰብሳቢ ይዟል፡፡

በሌላ በኩል ከተሰብሳቢው ውስጥ በ6 ቢሮዎች የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈፀሚያ በጀት (SDG) የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 2,163,454,872.95 (21.88%) ሲሆን በ2008 በጀት ዓመት ከነበረው ተመሳሳይ የበጀት ምንጭ ተሰብሳቢ ሂሳብ ጋር በጥቅል ሲነፃፀር 3% የጨመረ መሆኑን ያሳያል፡፡

ስለሆነም ሂሳቡ በእድሜ ተተንትኖ ያልተያዘ በመሆኑ ምን ያህሉ ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ ማረጋገጥና በ2008 በጀት ዓመት ከነበረው የተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ምን ያህሉ እንደተወራረደ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ ምን ያህል እንደተጨመረ ተለይቶ በሪፖርቱ በዝርዝር ያልተገለጸ በመሆኑ በዝርዝር አስተያየት ለመስጠት ባያስችልም የ2009 በጀት ዓመት የተሰብሳቢ ሂሳብ በ2008 በጀት ዓመት ከነበረው የተሰብሳቢ ሂሳብ ጋር በጥቅል ሲነፃፀር በብር 11.63% ጭማሪ አሳይቷል፡፡

ስለሆነም እየተወሰደ ያለው እርምጃ (በመሰብሰብ፣ በማወራረድ ብሎም በማስወገድ) አዝጋሚ በመሆኑ ሂሳቡ በዕድሜ ተተንትኖ እንዲያዝ በማድረግ መወራረድ የሚችለውን ሂሳብ ማወራረድ እንዳለበትና ምክንያቱ ተጣርቶ ሊሰበሰብ የማይችለውን ደግሞ ቀደም ሲል በወጣው የሂሳብ አያያዝ መመሪያ መሰረት ከመዝገብ ሊሰረዝ እንደሚገባ በዝርዝር አስገንዝበናል፡፡

**በክልሉ በተከፋይ የተያዘ ሂሳብ፤**

18. በክልሉ ውስጥ በአጠቃላይ የሚገኘውን የተከፋይ ሂሳብ ብር **5,814,939,698.85** ሲሆን ይህ ሂሳብ ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየና በ2008 በጀት ዓመት ተይዞ ከነበረው የተከፋይ ሂሳብ ውስጥ ምን ያህሉ እንደተወራረደና በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተጨመረውን በመለየት አስተያየት ለመስጠት በሚያስችል መንገድ አልተያዘም፡፡ ከዚህ ተከፋይ ውስጥ **56.47%** በመንግስት መ/ቤቶች ሌሎች በሚል የተያዘ ተከፋይ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በ6 ቢሮዎች የተያዘው የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈፀሚያ በጀት /SDG/ ተከፋይ ሂሳብ ብር 752,382,146.05 ከጠቅላላው የተከፋይ ሂሳብ 12.94% የያዘና ከ2008

በጀት ዓመት የተከፋይ ሂሳብ ጋር በጥቅል ሲነፃፀር 14% የጨመረ መሆኑን ያሳያል፡፡ እንዲሁም በአጠቃላይ የ2009 በጀት አመት የተከፋይ ሂሳብ በ2008 በጀት አመት ከነበረው ጋር በጥቅል ሲነፃፀር 15.8% ጭማሪ አሳይቷል፡፡

ስለሆነም የደመወዝ ተከፋይ፣ የጡረታ ተከፋይ፣ ሌሎች የደመወዝ ተቀናናሾች፣የንግድ ስራ ትርፍ ግብር፣ በገዥው ተይዞ የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ ተከፋይ ለሚመለከታቸው ወቅቱን ጠብቆ ያለማስተላለፍ ምክንያት የተፈጠረ ተከፋይ ሲሆን ሂሳብ በእድሜ ተተንትኖ ሊያዝና በየወቅቱ መከፈል የሚችለውን ሂሳብ ለሚመለከታቸው ሊከፈልና ምክንያቱ ተጣርቶ ሊከፈል የማይችለው ሂሳብ ደግሞ ወደ ሀብትነት ተቀይሮ ስራ ላይ እንዲውል አሳስበናል፡፡

**የተፈጥሮ ሚዛኑን ያልጠበቀ ሂሳብ፤**

19. በቢሮው የተጠቃለለው የሪፖርት አቅራቢ መ/ቤቶች ሁሉም ሂሳቦች መደበኛ ሚዛን ያላቸው ለመሆኑ በናሙና የተመረጡ ሪፖርት አቅራቢዎች (በከተማ አስተዳደሮች እና ወረዳዎች) የሂሳብ ሪፖርት ሲታይ የተፈጥሮ ሚዛኑን ያልጠበቀ የመደበኛ በጀት ሂሳብ ላይ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 59,514.96 እና የተከፋይ ሂሳብ ብር 1,187,799.45 በድምሩ ብር 1,247,314.41 የተፈጥሮ ሚዛኑን ሳይጠብቅ ተመዝግቦና ሪፖርት ተደርጎ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም ስለተዘጋጀው አመታዊ ሪፖርት ትክክለኛ መረጃ የማይሰጥና በተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥር በመሆኑ የሪፖርቱን ትክክለኛነት የተዛባና አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም ምክንያቱን በማጣራት ተገቢው የማስተካካያ እርምጃ ሊወሰድ እና ለወደፊቱም የሪፖርት አቅራቢ መ/ቤቶች ወርሃዊ ሪፖርታቸውን ለቢሮው በሚያቀርቡበት ጊዜ ሁሉም ሂሳቦች መደበኛ ሚዛናቸውን የጠበቁ መሆኑ እየተረጋገጠ ሊሆን እንደሚገባ በሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

**በብልጫ ሪፖርት የተደረገ የተጣራ ሃብት ሂሳብ፤**

በቢሮው የቀረበው የተጠቃለለ ፈንድ የሀብትና እዳ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተጣራ ሀብት ብር 9,450,176,028.01 የሚያሳይ ቢሆንም ትክክለኛነቱ በኦዲት ሲጣራ ወደ 2010 በጀት ዓመት ሊዛወር የሚገባው የተጣራ ሀብት ብር 8,711,995,309.52 በመሆኑ በሪፖርት የተላለፈው የተጣራ

ሀብት በብር 738,180,718.49 (በ7.8%) የተጣራ ሃብት በብልጫ ተይዞና ተላልፎ ተገኝቷል፡፡

ልዩነቱ ክልሉ ያለውን የተጣራ ሃብት አላግባብ ከፍ አድርጎ የሚያሳይ እና በሪፖርቱ መሰረት ውሳኔ የሚያስተላልፉ አካላትን የሚያሳስት ስለሆነ የልዩነቱ ምክንያት በዝረዝር ተለይቶና የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ በዝርዝር በማናበብ በሀብት የተከፈለ የገቢ ተመላሽ ካለ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በኦዲት ሪፖርቱ አሳስበን ቢሮው በሪፖርቱ ላይ በሰጠው ግብረ መልስ በሁሉም ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጅ ለመውሰድ በየደረጃው እየተደረጉ ያሉትን ጥረቶች የገለጸ ሲሆን በተለይም በተሰብሳቢና በተከፋይ ሂሳብ ላይ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት በየወረዳዎች አጣሪ ኮሚቴ ተዋቅሮ እየተሰራ እንደሆነ አብራርቷል፡፡

**ክብርት አፈ-ጉባዔ!**

**የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

**መ/ቤታችን ከጥር 2010 እስከ ግንቦት 30/2011 ባለው ጊዜ ያከናወነውን የ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ውጤት ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡**

20. መ/ቤቱ በዚህ ሪፖርት ያካተተው የ295 መ/ቤቶች የ2010 በጀት ዓመት የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት እና ያለፉት ዓመታት የኦዲት ውጤቶች እርምጃ አወሳሰድ የክትትል ሪፖርት ውጤት ነው፡፡የ2010 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በአወቃቀር እርከን ሲታይ በክልል/ ማእከል 99(34%)፣በዞን 12(4%)፤ በከተማ አስተዳደሮች 88(30%) ቀሪዎች 96(32%) በወረዳ ደረጃ ያሉ ናቸው፡፡

21. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብትና ሰነዶች፣ የሂሳብ መግለጫዎች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የሚመለከታቸው ሰራተኞች እና ኃላፊዎች የሰጧቸው ማብራሪያዎች ናቸው፡፡ከዚህም በተጨማሪ ከ3ኛ ወገኖች የተገኙ ብቃትና ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች ሥራ ላይ ውለዋል፡፡ የመ/ቤቶቹን ሂሳብ ኦዲት ማድረግ የመ/ቤታችን ኃላፊነት ሲሆን የሂሣብ መግለጫዎች የማዘጋጀት፣ ኦዲት የማስደረግና የሥሩበትን ሁኔታ የማስረዳት እንዲሁም በኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ እርምጃ መውሰድ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊነት ነው፡፡ ከኦዲት ስልት አንፃር ከ295 መ/ቤቶች ውስጥ 235(79.66%) በንሞና እንዲሁም 60(20.34%) መ/ቤቶች በልዩ ኦዲት ጥቆማ በዝርዝር ኦዲት የተደረጉ ናቸው፡፡

**የኦዲት አስተያየት** የ2010 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ 295 መ/ቤቶች መካከል የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው 235 መ/ቤቶች ናቸው፡፡ለ25 (8%)***"ንፁህ የኦዲት አስተያየት"***፣ ለ204 (69%)**"ከዚህ በስተቀር"**፣ ለ1 (1%) ***"አጥጋቢ አይደለም"***፣ ለ5(2%) መ/ቤቶች **"አስተያየት መስጠት አልተቻለም"**የሚል የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ የኦዲት አስተያየቱ ከ2009 በጀት ዓመት የሂሳብ ኦዲት ጋር ሲነፃፀር " **ንፁህ አስተያየት የሚለው"** በ79% መጨመሩ በአንዳንድ መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዙ እና የሀብት አስተዳደር ስርዓቱ እየተሻሻለ መምጣቱን የሚያሳይ ሲሆን የኦዲት አስተያየት የማይሰጥበት የልዩ ኦዲት ሂሣብ ደግሞ በ15% መቀነሱ ህብረተሰቡ ብልሹ አሰራሮችን የመታገል ልምዱ እና ስጋትን መሰረት አድርጎ ኦዲትን የመፈፀም ትኩረት እያደገ የመጣ ቢሆንም በዚህ በጀት ዓመት በአንዳንድ ልዩ ኦዲቶች ውስብስብ ባህሪነት የተነሳ ድርጊቱን ለመፈለግ ከፍተኛ ጊዜ ስለወሰደ የመፈፀም አቅም ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩን ያመላክታል፡፡

የገንዘብ አያያዝና አስተዳደሩም ሆነ የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱን መርምሮ ተዓማኒና በቂ የሂሳብ አያያዝና አስተዳደር መኖሩን ለማረጋገጥና የሙያ አስተያየት ለመስጠት ያላስቻሉ ጉልህና መሰረታ

ችግር የተገኘባቸው በመሆኑ **"አስተያየት መስጠት አልተቻለም"** የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው መ/ቤቶች፡ደቡብ አቸፈር ወረዳ እና ሊቦ ከምከም ወረዳ፣መቅደላ ወረዳ፣ሚዳ ወረሞ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከላት እና አምበር ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት ናቸው፡፡

መንግስት የመደበላቸውን ሀብት/ገንዘብ በአግባቡና ህጉ በሚፈቅደው አሰራር መሠረት ስራ ላይ ያላዋሉ፤ የማጭበርበር ተንኮል የተፈፀመባቸው፤ጉልህና መሠረታዊ ግኝቶችና የአሰራር ችግሮች የተስተዋሉባቸው በመሆኑ **"አጥጋቢ አይደለም"** የሚል አስተያየት የተሰጠው መ/ቤት ደግሞ ደላንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ነው፡፡

## የኦዲት ሪፖርቶች ምላሽ አሰጣጥ

22. በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉት 235 መ/ቤቶች መልስ ያልሰጡት 48(20.42%) መ/ቤቶች ናቸው፡፡ የዚህ ዓመት መልስ አሰጣጥ ካለፈዉ በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር እየተሻሻለ የመጣ በመሆኑ የፋይናንስ ግልጽ አሰራርና የተጠያቂነት ሥርዓት እየዳበረ መሄዱን የሚያመላክት ቢሆንም አሁንም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ በኩል እጥረቶች እንዳሉባቸው ያሳያል፡፡ ምላሽ ያልሰጡ መ/ቤቶችም፤

**ክልል/ማዕከል**

1. ፀዳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ
2. በጌ ምድር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ
3. ዳንግላ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል
4. ባህር ዳርና አካባቢዋ ከፍ/ፍ/ቤት
5. ንግድ፣ኢንዱስትሪና ገበያ ልማት ቢሮ
6. አብክመ ፖሊስ ኮሚሽን
7. ትምህርት ቢሮ
8. እንጅባራ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ

2. ምዕራብ ጎጃም ዞን አስተዳደር

9. ጅጋ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ
10.ቡሬ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ
11.ደንበጫ ከተማ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ
12.ፍኖተ-ሰላም ከተማ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ

**ምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳዳር**

13.አማኑኤል ጤና አጠባበቅ ጣቢያ
14.ደብረ ማርቆስ ከተማ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ
15.አነደድ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
16.ደ/ማርቆስ ከተማ አስ/ገቢዎች ጽ/ቤት
17.ምስራቅ ጉጃም ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
18.አምበር ከተማ ውሃና ፍሳስ አገልግሎት ጽ/ቤት

**ሰሜን ጎንደር ዞን አስተዳደር**

19.ጣቁሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
20.ሰሜን ጎንደር ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
21.ዳባት ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል-2010

**ደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር**

22.ወረታ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት
23.ሊቦ ከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ደ/ስ/ማዕከል
24.ፎገራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
25.ደቡብ ጎንደር ዞን ፖሊስ መምሪያ

**አዊ ብሄረሰብ ዞን አስተዳደር**

26.ቲሊሊ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ
27.እንጅባራ ጤና አጠ/ ጣቢያ
28.ዳንግላ ከተማ ጤና አጠ/ ጣቢያ
29.እንጅባራ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት

**ደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር**

30.መሃል ሳይንት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
31. ቦረና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
32.አምባሰል ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
33.ሳይንት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
34.ለጋምቦ ወ/ነ/ፋ/ድ/ማ
35.አርጎባ ብሄረሰብ ልዩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል

36.ወረኢሉ ከ/አስ/ነ/ፋ/ድ/ማ
8. ኦሮሞ ብሄረሰብ ዞን አስተዳደር
37.ደዋ ጨፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
38.ባቲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
**ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር**
39.አለም ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
40.ደብረ ብርሃን ከተማ አስ/ገቢዎች ጽ/ቤት
41.አሳግርት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
42.ምንጃር ሸንኮራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
43.መንዝ ጌራ ምድር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
44.ቀወት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
45.አንኮበር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
46.መሃል ሜዳ ከተማ/አስ/ነ/ፋ/ድ/ማ
**ሰሜን ወሎ አስተዳደር**
47.ግዳን ወ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
**ዋግኽምራ ብሄረሰብ ዞን አስተዳደር**
48.ዳህና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ ናቸው፡፡

## የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ውጤት

### የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

23. የ2010 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች በድምሩ ብር 3,321,989.12 ጉድለት የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 2,537,381.99 ከቀድሞ ገ/ያገሮች የተገኘ ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ (ሰኔ 30) በጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ መከታተያ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበት እና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲነጻጸር በ10 መ/ቤት ብር **3,712,513.03** የተቆጠረ ገንዘብ ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በማነስ እና በ1 መ/ቤት ቆጠራ ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በመብለጥ ብር 47,196.51 ተስተውሏል፡፡

ከጥሬ ገንዘብ ጉድለቱ ብር 200,811.99 (6%) የተተካ ሲሆን ቀሪው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ሰኔ 21/2011ዓ.ም ድረስ ግብረ-መልስ ባለመምጣቱ የተወሰደውን እርምጃ ማወቅ አልተቻለም፡፡

### የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ማድረግ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች

24. በ56 (23.83%) መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2010 ዓ.ም ላይ ያለውን የጥሬገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፤ (ዝርዝራቸው በዋናው ዘገባ ሪፖርት ተመልክቷል፤)

## የገቢ ሒሳብ ኦዲት ውጤት

### የማጭበርበር ወንጀል የተፈፀመበት *የገቢ ሂሳብ እና ዘዴዎች፣*

25. በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ2 መ/ቤቶች ብር 1,455,423.90 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡ማጭበርበሩ የተፈጸመባቸው መ/ቤቶችና ዘዴዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- **ዳሸን ቢራ ፋብሪካ አክሲዮን ማህበር ብር** 1,453,923.90 ዱየት ቢቬሬጅ አፍሪካ ሊሚትድ ካምፓኒ ከዳሸን ቢራ ፋብሪካ አ/ማህበር አዲስ የአክሲዮን ድርሻ ለመግዛት በፈፀመው ውል ስምምነት መሰረት 90,000,000.00 ዶላር ኢንቨስትመንት የገዛ ሲሆን ከዚህ ገንዘብ ውስጥ 89,622,610.07 ዶላር በዳሸን ቢራ ፋብሪካ አክሲዮን ማህበር ስም በተከፈተ የባንክ አካውንት ቁጥር ገቢ የተደረገ ሲሆን እና 326,285.03 ዶላር አሳማኝ ምክንያት ባይቀርብለትም ‹‹ለደብረ ብርሀን ቢራ ፋብሪካ ፕሮጀክት ለማማከርና ጨረታ ግምገማ ተከፍሏል›› በሚል ተቀናንሶ የተገኘ ስለሆነ 51,104.90 ዶላር ወይም በወቅቱ የገንዘብ ምንዛሬ(1 ዶላር ለ28.44987) መሰረት ብር 1,453,923.90 ገቢ ሳይደረግ ለግል ጥቅም ውሎ የተገኘ፣
- **አምባሰል ወረዳ ሁሉን አቀፍ የህዝብ መረጃ ማዕከል ማህበር ብር** 1,500.00 በዋናው የገቢ ደረሰኝ ቅጠል ላይ በወቅቱ በማህበሩ ባልተቀጠረ ገንዘብ ያዥ ስምና ፊርማ በማስመሰል በቀሪው ደግሞ ምንም ባለመፃፍ የማጭበርበር ድርጊት ተፈጽሞ ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ፣ናቸው፡፡

በመሆኑም ድርጊቱን ከፈጸሙት አካላት የሚፈለገው የህዝብ ሀብት ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ብናሳስብም የክስ ሂደቱ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አልተገለፀልንም፡፡

**ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ተሰብስቦ ለግል ጥቅም የዋለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ፣**

26. የተጨማሪ እሴት ታክስን አስመልክቶ በወጡ ደንብና መመሪያዎች መሠረት ማንኛውም በተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ደረጃ የሚገኝ ድርጅት በከፋይነት ተመዝግቦ እቃ/አገልግሎት ሲያቀርብ ለከፍያው የቫት ደረሰኝ/ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ ያለበትና ግዥ የሚፈጽሙ አካላትም ክፍ ከመፈጸማቸው በፊት የቫት ደረሰኝ ማስረጃው እንዲቀርብላቸው የማድረግ ሃላፊነት የተጣለባቸው ቢሆንም በ2 መ/ቤቶች ብር 263,430.21 የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብለት ክፍያ ተፈጽሞ የተጨማሪ እሴት ታክሱ ለመንግስት ገቢ ሳይሆን ተገኝቷል፡-
    - **ዳባት ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 147,709.70 ለከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት የአሸዋ ግዥ ሲፈፀም እና የዲች ግንባታ ስራ ለአከናወኑ የስራ ተቋራጮች ክፍያ ሲፈጽም ለመንግስት ገቢ ያልሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣
    - **ሊቦ ከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 115,720.51 የአስተዳደር ጽ/ቤት የመፀዳጃ ቤት፣ የአዳራሽ እና የቢሮ ግንባታ እንዲሁም የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም የጽ/ቤት የቢሮ ግንባታ ለአከናወነው ተቋራጭ ክፍያ ሲፈፀም ለመንግስት ገቢ ያልሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣

    ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ተሰብስቦ ለግል ጥቅም የዋለ በመሆኑ ተቋራጮች ታክሱን ለገቢ ሰብሳቢው አካል ገቢ አድርገው ማስረጃ እንዲያቀርቡ

መደረግ እንዳለበት እያስገነዘብን ታክሱን ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆኑ በሚመለከተው የፍትህ አካል ክስ በመመስረት ከተጠቃሚው የተሰበሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ ወደ መንግስት ካዝና ገቢ የሚሆንበት ሁኔታ እንዲመቻች በሪፖርታችን ብናሳስብም የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ አልደረሰንም፡፡

**ያልተሰበሰበ (በውዝፍ) የሚገኝ ገቢ፤**

27. የ2010 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ 295 መ/ቤቶች በ89ኙ ብር 154,154,046.04 ስራ ላይ ባለው የገቢ አሰባሰብ ስርዓት መሠረት በወቅቱ ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ ሰሜን ጎንደር ዞን አስተዳደር ብር 40,856,831.73(27%)፣ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳዳር ብር 34,077,605.93 (22%)፣ ባህር ዳር ከተማ አስተዳር ብር 19,555,242.56(13%)፣ምዕራብ ጎጃም ዞን አስተዳደር ብር 16,111,967.61(10%) እና ደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር ብር 9,229,282.88 (6%) ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ::

ያልተሰበሰበ ገቢ ተብሎ ከተያዘው ዉስጥ ብር 1,675,628.47 (1%)ብቻ ስለመሰብሰቡ በተሰጠው የኦዲት ሪፖርት ግብረ መልስ የተገለጸ ሲሆን ቀሪው የተሰበሰበ ስለመሆኑ ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ሰኔ 21/2011 ዓ/ም ድረስ መልስ ያልተሰጠበት ነው፡፡

**ያልተሰበሰበ 2% የንግድ ትርፍ ግብር፤**

28. በገቢ ግብር አዋጅና ደንብ እንደተመለከተው ከተወሰነ መጠን በላይ የሆነ የእቃና አገልግሎት ክፍያ ሲፈጸም ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ መሰሠብሰብ የሚገባው 2% የንግድ ስራ ትርፍ ግብር ከ4 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 179,536.21 ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ገቢው ከየሚመለከታቸው ላይ ክትትል ተደርጎ እንዲሰበሰብ በየሪፖርቶቹ ባሳሰብነው መሰረት መሰብሰቡን የሚገልጽ ማስረጃ በግብረ መልስ ያልተገለፀ በመሆኑ ያልተሰበሰበው የንግድ ስራ ትርፍ ግብር በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ለማወቅ አልተቻለም፡፡

**ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች**

29. ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሟልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ21 መ/ቤቶች ብር 94,077,151.66 የያዙ የገቢ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡የገቢ ደረሰኞችን ለኦዲት ካላቀረቡት መ/ቤቶች መካከል ከብር 1,000,000.00 በላይ የገንዘብ መጠን በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ከሚወስዱ መ/ቤቶች መካከል፤

ኮምቦልቻ ከተማ አስ/ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 32,527.246.66 የያዙ፣ ወልዲያ ከተማ አስ/ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 16,713,985.12 የያዙ፤ኮምቦልቻ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 15,952,423.72 የያዙ፣የደቡብ አቸፈር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 4,177,337.32 የያዙ፣ከሚሴ ከተማ አስ/ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 3,739,296.92 የያዙ፣ከሚሴ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 3,721,438.70 የያዙ ፣የጃቢ ጠህናን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 3,550,006.94 የያዙ፤ የባሶና ወራና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 2,117,415.00 የያዙ፣ አንጎለላና ጠራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ ስ/ማዕከል ብር 1,881,964.46 የያዙ፤ አምባሰል ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,175,573.19 የያዙ፤ ሰሜን ሜጫ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,027,299.74 የያዙ፣የስፖርት ም/ቤት ደረሰኞች፣ የመደበኛ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፤ የመሬት መጠቀሚያና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ የእንስሳት ጤና ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ለኦዲት ስራ አልቀረቡም፡፡

ለኦዲት ስራ ባልቀረቡት ደረሰኞች ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ባለመረጋገጡ በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለመስጠት ገደብ የተጣለበትና ማጭበርበር ተሰርቶባቸው ይሆናል የሚል ጥርጣሬን ያሳደረ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች የገቢው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥና ደረሰኞቹን በሰወሩ/ባላቀረቡ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በየሪፖርቶቹ ባሳሰብነው መሰረት ብር 816,613.73(0.87%) የያዙ ገቢ ደረሰኞች ብቻ ለውስጥ ኦዲት ቀርበው የተረጋገጡ ስለመሆናቸው በተሰጠው የኦዲት ሪፖርት ግብረ መልስ የተገለጸ ሲሆን ለቀሪው ብር 93,260,537.95 የተወሰደው እርምጃ እስከዚህ ሪፖርት ጥንቅር ሰኔ 21/2011 ዓ/ም ድረስ ምላሹ አልተገለፀም፡፡

**የተሰብሳቢ ሂሣብ ኦዲት ውጤት**

**በወቅቱ ያልተሰበሰበ (ያልተወገደ) ተሰብሳቢ ሂሣብ**

30. የ2010 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ92 መ/ቤቶች ብር 865,021,013.48 በወቅቱ የፋይናንስ አሠራር ስርዓት መሠረት ሣይሰበሰብ/ከመዝገብ ሳይሰረዝ ተገኝቷል፡፡

ተሰብሳቢ ሂሳቦች የራሳቸው የተወሰነ የመሰብሰቢያ/የመወገጃ ጊዜ እንዳላቸውና በመመሪያው መሠረት ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በቢሮው በቁጥር 6/2004 በክፍል 4 በተላለፈው መመሪያ የተገለጸ ቢሆንም አንዳንድ መ/ቤቶች ተግባራዊ ባለማድረጋቸው ጊዜው በዘገየ ቁጥር ያለመሰብሰብ ዕድሉ እየሠፋ ስለሚሄድ መመሪያው በሚያዘው መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርቶቻችን ባሳሰብነው መሰረት ስለተወሰደው እርምጃ በተሰጠው ምላሽ ብር 138,944,758.89(16%) ከኦዲት በኋላ የተሰበሰበ መሆኑ የተገለፀ ሲሆን በቀሪው ላይ ስለተወሰደው እርምጃ ባለመገለጹ ይህ ዘገባ እስከተሰራበት ሰኔ 21/2011 ዓ.ም

ድረስ ተሰብሳቢ ሂሳቡ ስላለበት ደረጃ የታወቀ ሁኔታ የለም፡፡

31. በሌላ በኩል የተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኛነት እንዳስፈላጊነቱ በኦዲት ወቅት በሚመለከተው 3ኛ ወገን ማረጋገጫ እንዲቀርብለት የሚደረግ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ስለትክክለኛነቱ ከ3ኛ ወገን (ይሰበሰብባቸዋል ተብሎ ከተያዙ አካላት) ለማረጋገጥ ከተጠየቁት የተሰብሳቢ ሂሳቦች መካከል በ4 መ/ቤቶች ብር 11,160,917.53 የ3ኛ ወገን ማረጋገጫ አልቀረበለትም፡፡

ከላይ ከተመለከተው ተሰብሳቢ መካከል በ1 መ/ቤት ብር 188,488.43 ትክክለኛ ተሰብሳቢ ሂሳብ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ሠነድ፣ መቼ እንደተሰጠ፣ ከማን እንደሚሰበሰብ እና ለምን እንደተሰጠ የሚያሳይ ማስረጃ ሳይኖር በመቅደላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ለሂሳቡ ትክክለኛ ዝርዝር ደጋፊ ማስረጃ ካለ ተጣርቶ በየባለዕዳዎቹ ስም ተለይቶ እንዲያያዝና ክትትል ተደርጐ እንዲሰበሰብ ወይም በመመሪያው መሰረት ከመዝገብ እንዲሰረዝ የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ ሆኖም ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ሰኔ 21/2011 ዓ.ም ድረስ የተወሰደውን እርምጃ የሚገልጽ ምላሽ አልደረሰም፡፡

32. በወቅቱ ካልተሰበሰበው የተሰብሳቢ ሂደ,ሳብ መካከል በ14 መ/ቤቶች ብር 187,513,514.93 የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመተላለፍ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡ ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለትን ተሰብሳቢ ሂሣብ በተመለከተ ገንዘቡ ከማን እንደሚፈለግ በባለቤቱ ስም ተለይቶ በሚያሳይ መልኩ የተመዘገበ ባለመሆኑና በጥቅሉ ስለተመዘገበ ባለቤቱን አውቆ ከሚመለከተው ላይ ለመሰብሰብ/ለማስወገድ የማያስችል በመሆኑ የተሻሻለውን የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት በመከተል በየስሙ የተቀፅላ ሌጀር ሊዘጋጅለትና ክትትል እየተደረገ ሊሰበሰብ/ከመዝገብ ሊሰረዝ/ እንደሚገባው በሪፖርታችን ብናሳስብም ከዚህ ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ በግብረ መልስ ብር ብር 6,961,488.33(3.7%) ተቀጽላ ሌጀር የተዘጋጀለት መሆኑ የተገለፀ ሲሆን ቀሪው ሂሳብ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ሰኔ 21/2011 ዓ.ም ድረስ የተሰጠ ግብረ መልስ ባለመኖሩ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አልታወቀም፡፡

**የወጪ ሒሣብ ኦዲት ውጤት፤**

***የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት የወጪ ሂሳብ እና ዘዴዎች***

33. በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች መካከል በ10 መ/ቤቶች ብር 26,537,407.04 የተለያዩ የማጭበርበር ድርጊቶች ተፈፅሞበት ተገኝቷል፡፡የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀ መባቸው መ/ቤቶችና ዘዴዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- **ዳሽን ቢራ ፋብሪካ አክሲዎን ማህበር ብር 23,541,629.32** አላግባብ በተፈፀመ የውል ስምምነት ምክንያት ዱየት ቢቬሬጅ አፍሪካ ሊሚተድ ካምፓኒ ለራሱ የኢንቨስትመንት ውሳኔ የሚረዳው

የአዋጭነት ጥናት ያስጠናበትን ወጭ ዳሽን ቢራ ፋብሪካ አክሲዎን ማህበር አላግባብ እንዲሸፍን የውል ስምምነት በመፈፀም ተከፍሎ የተገኘ ብር 11,408,981.50፣

ለፒቲ ኤስ ፐሮሰስ ሶሉሽን የደብረ ብርሀን ቢራ ፋብሪካ ፕሮጀክት የጨረታ ግምገማ እና የማማከር ስራ የሰሩበት በሚል በዳሽን ቢራ ፋብሪካ አክሲዎን ማህበር ስም በሲውዘርላንድ አገር በሚገኘው በርክሌይ ባንክ ከተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር 62659307 ዳሽን ቢራ ፋብሪካ አክሲዎን ማህበር ከአማካሪ ድርጅቱ ጋር የተዋዋለበት የስራ ዝርዝር፣የውል ስምምነት፤ለተከናወነው ስራ የሚያሳይ ሪፖርት እና ክፍያው በትክክል ለድርጅቱ የተከፈለ መሆኑን የሚያሳይ የክፍያ ደረሰኝ ሳይቀርብ (አጠቃላይ ለክፍያው አንዳችም ማስረጃ ሳይኖር) ተከፍሎ የተገኘ ብር 6,066,323.91፣

ይህ በእንዲህ እንዳለ ለዚሁ ተግባር ያለማስረጃም ቢሆን ክፍያው ተፈጽሞ እያለ ለዚሁ አማካሪ ድርጅት ተመሳሳይ የማማከርና የጨረታ ግምገማ ለሰራበት በሚል በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በዳሽን ቢራ ፋብሪካ አክሲዎን ማህበር ስም በተከፈተ የይሮ አካውንት ቁጥር 1000037399543 ላይ ብር 6,066,323.91 አላግባብ በድጋሜ ተከፍሎ የተገኘ፤

- **ከለላ ከተማ መሪ መዘጋጃ ቤት ብር 1,448,614.75** በከተማው የውስጥ ለውስጥ መንገድ ለማሰራት የማሽነሪ ኪራይ ውል ተይዞ ወደ ስራው የተገባ ሲሆን የተጨማሪ የስራ ውል እና ስራው ለመሰራቱ የባለሙያ ማረጋገጫ ሳይኖር ያለአግባብ በብልጫ ተከፍሎ ለግል ጥቅም የዋለ፣
  - **አማራ መንገድ ስራዎች ድርጅት ብር 844,800.00** በመደበኛ በጀት ለሚገነባው ለሞላሌ፣መቅደላ እና ጃዊ ሆስፒታሎች ግንባታ የሚውል ሴራሚክ ግዥ ለመፈፀም በወጣው ውስን ጨረታ ኬኤኤም የግል ድርጅት ዝቅተኛ ዋጋ ለካሬ ሜትር ብር 232.00 አቅርቦ ከተመረጠ በኂላ ያቀረበው ሴራሚክ የጥራት ጉድለት ያለበት ሆኖ በመገኘቱ ጨረታው ውድቅ ከተደረገ በኂላ ነገር ግን ይህ ድርጅት ለሌላ የልማት ድርጅት ለከተሞች ልማት አክሲዎን ማህበር ጥራት ያለው ሴራሚክ አቅርቧል ተብሎ በካሬ ሜትር ብር 320.00 ሂሳብ በቀጥታ የግዥ ዘዴ በመገዛቱ ውስን ጨረታ ወጥቶ ስምምነት ከተደረሰበት ዋጋ በላይ ብር 844,800.00=(320-232) Xብዛት 9600) አላግባብ በብልጫ የተከፈለ፣
  - **ባቲ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 182,276.00** በከተማ አስተዳደሩ የመግስት ሰራተኞች ላልሆኑ እና ማንነታቸው በማይታወቅ ግለሰቦች ስምና ላልተሰራ ስራ አላግባብ ተከፍሎ ለግል ጥቅም የዋለ የውሎ አበል ሂሳብ፣
  - **መተማ ወረዳ ሽንፋ መሪ መዘጋጃ ቤት ብር 170,082.46** የሽንፋ ከተማ የፍትህ ጽ/ቤት እና ፍርድ ቤት ቢሮ ግንባታ ሲከናወን ላልተሰሩ እና ተጀምረው ላላለቁ ስራዎች አላግባብ በብልጫ የተከፈለ እና ለግል ጥቅም የዋለ የግንባታ ስራ ክፍያ፣
  - **ከሚሴ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 166,239.39** አገልግሎት ጽ/ቤቱ በ04 ቀበሌ የድሃ ድሃ

ቤት ለተሰራበት ክፍያ ሲፈፀም ከውለታ በላይ አለአግባብ በብልጫ ተከፍሎ ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ ብር 38,286.38 ፣በከተማው ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች የመንገድ ጠረጋ ስራ ሲከናወን በውለታ መሰረት የ232.30 ሰዓት መከፈል ሲገባው የ300 ሰዓት በመከፈሉ በብልጫ 67.7 ሰዓት በብር 1890.00 ለሰዓት በብልጫ ተከፍሎ ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ ብር 127,953.00፣

- ***ዳንግላ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 110,808.39*** የሶዴም ላምፕና አርሞች ግዥ እዲፈፀም ዲዛይንና እስፔሲፊኬሽን ከተዘጋጀ በኋላ ከተዘጋጀው መስፈርት ውጭ በተመሳሳይ ዋጋ ሜርኩሪ አምፑል ተገዝቶ ገቢ በመደረጉ ተፈላጊውን ጥቅም ሳይሰጥ ለብልሽት የተዳረገ ላምፕና አርሞች ግዥ፣
- ***አማራ ውሀ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት-ግልገል አባይ መስኖ ፕሮጀክት ብር 44,584.35*** በግልገል አባይ መስኖ ፕሮጀክት የሳይክሎፒያን አርማታ፣የግንባታ ስራ፣የብረት አርማታ እና የማስ ኮንክሪት ስራዎች ግንባታ ሲከናወን ሆን ተብሎ ከአካባቢ የመስሪያ ዋጋ በላይ በብልጫ ተከናውኖ ለግል ጥቅም

የዋለ የብረት መቁረጥ፣ማንጠፍና ማሰር ስራ፣

- ***መርጦለማሪያም ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ብር 16,053.23*** መስክ ሳይወጣ በመደበኛ ስራ ላይ ቢሮ ውስጥ እያሉ መስክ እንደተወጣ ተደርጎ አላግባብ የተከፈለ እና ለግል ጥቅም የዋለ ውሎ አበል፣
- ***ራያ ቆቦ ወረዳ ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት ብር 12,319.15*** ለአንድ የጽ/ቤቱ ሰራተኛ ከሐምሌ/2006-ህዳር/2008 ድረስ አላግባብ በብልጫ ተከፍሎ ለግል ጥቅም የዋለ የደመወዝ ሂሳብ ብር 9,303,.15፣ ለአንድ የጽ/ቤቱ ሰራተኛ ብር 2,008.00 መከፈል ሲገባው ብር 2,298.00

በመከፈሉ አላግባብ በብልጫ ተከፍሎ ለግል ጥቅም የዋለ የደመወዝ ሂሳብ ብር 3,016.00፣

በመሆኑም ድርጊቱን ከፈጸሙት ኃላፊዎች እና ሰራተኞች የሚፈለገው የህዝብ ሀብት ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ብናሳስብም በምን ደረጃ ላይ እንዳለ አልተገለፀልንም፡፡

### ለሚመለከተዉ ፈሠስ ሳይደረግ የቀረ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤

34. በ11 መ/ቤቶች ለስራ ተቋራጮች የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 3,027,011.70 በትክክል ለሚመለከተዉ ገቢ ሠብሳቢ መ/ቤት ፈሠስ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብለት ተገኝቷል፡፡ ገንዘቡ በወቅቱ ፈሠስ መደረጉ ክትትል ባለመደረጉ ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ተሰብስቦ ለረዥም ጊዜ በታክሱ ሰብሳቢዎቹ እጅ እየተያዘ ለስራ ማስኬጃ የሚውልበትና ከጊዜ ብዛትም ፈሰስ የማይደረግበት ሁኔታ በመኖሩ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ለግብር አስገቢው መ/ቤት ፈሰስ መደረጉ እንዲረጋገጥ ሆኖ

ለወደፊቱም በክልል ደረጃ የተጀመረው የመንግስት ተቋማት ታክስን ከክፍያ ላይ ቀንሶ የማስቀርት አሠራር እስከታችኛው አደረጃጀት ድረስ እንዲወርድ በሪፖርታችን ብናሳስብም የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ አልደረሰንም፡፡

**አላግባብ የተፈፀመ ክፍያ፤**

35. ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው በኦዲት ሲጣራ በ77 (26%) መ/ቤቶች የተለያየ ዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈፀም በብልጫ እንዲሁም የመስክ ስራ ላላከናወኑ ሠራተኞች የተከፈለ የውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በድምሩ ብር 7,869,866.10 አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ አላግባብ ከተከፈለው ክፍያ ከብር 300,000.00 በላይ ድርሻ ከሚይዙት መ/ቤቶች መካከል፡-

- **አጣየ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 858,674.30** ከመደበኛ በጀት ለቴክኒክና ኢንተርፕራይዝ ል/ጽ/ቤት የወጣቶች ልብስ ስፌት፣ብረታ ብረትና እንጨት ሥራ የሸድ ግንባታ ለተከናወነበት የ1ኛ እና 2ኛ ዙር ክፋያ ሲፈፀም እንዲሁም ከመስክ ቆይታ ቀናት በላይ ውሎ አበል ለሰራተኞች አለአግባብ በብልጫ ተከፍሎ የተገኘ፣
- **ሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 487,611.90** ለተለየዩ ቀበሌዎች የላቦራቶሪና መማሪያ ክፍል እና ቤተመጽሃፍት ግንባታ፤ የተፋሰስ ግንባታ የ1ኛ እና የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈጸም በብልጫ የተከፈለ ክፍያ እንዲሁም የተለያዩ የወረዳው ጽ/ቤቶች ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ እንደወጡ ተደርጎ ላልሰሩበት ስራ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል እና ከመመሪያ ውጭ ከከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት የተከፈለ የካሳ ግምት ክፍያ፣
- **ቦረና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 472,478.90** ከመደበኛ በጀት ለጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ከመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ መድሀኒት ሲገዛ በብልጫ የተከፈለ፣ከተራድኦ በጀት አላግባብበ የተከፈለ ውሎ አበል፣
- **ጎንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ብር 457,472.88** ለኮሌጁ ሰራተኞች ላልተሰራ ስራ የተከፈለ የትርፍ ስዓት ክፍያ፣ከታሪፍ በላይ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል፣
- **ደብረ ብርሃን ከተማ ውሀና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት ብር 397,608.00** ጽ/ቤቱ የተለያዩ የውሃ እቃዎችን በውድድር ሲገዛ አሸናፊ ከሆነው አቅራቢ ድርጅት መግዛት ሲገባው ከፍተኛ ዋጋ ከአቀረበው ድርጅት ግዥ በመፈፀሙ በልዩነት ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ የተፈፀመ ግዥ፣
- **ጃማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 342,670.50** ከእንስሳት ሃብት ማስፋፊያ፣ከሴፍቲኔት፣ከስፖርት ም/ቤት እና ከግሎባል ፈንድ ሂሳብ ለተለያዩ ሴክተር ሰራተኞች አላግባብ የተከፈለ የውሎ አበል፣

የ2010 በጀት ዓመት አላግባብ የተከፈለ ክፍያ ከ2009 በጀት ዓመት ብር 44,222,087.64 ጋር ሲነፃፀር

በመ/ቤት ቁጥር በ31 እና በገንዘብ መጠን በብር 36,352,221.54 ቀንሶ ተገኝቷል፡፡ አላግባብ ከተፈጸመው ክፍያ ውስጥ ብር 1,429,381.89 (18%) የተተካ ሲሆን ቀሪው ገንዘብ ስለመተካቱ ይህ ጥንቅር እስከተሠራበት ሰኔ 21/2011 ዓ.ም ድረስ ለመ/ቤታችን አልተገለጸም፡፡ይህም በተለያዩ መንገዶች አላግባብ ክፍያዎችን መፈጸም ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር እየተባባሰ መሆኑን ያሳያል፡፡

## የግንባታ ስራዎች ወጪን በተመለከተ፤

36. ማንኛውም የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት በባለሙያ እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው የግንባታ ክፍያ አፈፃፀም መመሪያን ባልተከተለ መንገድ በ43(14.6%) በድምሩ ብር 69,136,212.19 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ከዚህም ውስጥ ከብር 1,000,000.00 በላይ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች፡-

- ምዕራብ ጎጃም ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ለአስተዳደር ጽ/ቤት የቢሮ ግንባታ ሲከናወን ከ1-7ኛ ዙር ክፍያዎች ሲፈፀም የለውጥ ስራ ውል ከመጽደቁ በፊት ተከፍሎ የተገኘ የግንባታ ክፍያ ብር 26,782,352.41፣አዴት ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል በከተማው ውስጥ ለተፋሰስ ግንባታ ስራ፣ የተለያዩ ቀበሌዎች የቢሮ ግንባታ ስራ፣የአደባባይ ግንባታ ስራ፣የከብት ማድለቢያ ግንባታ፣ለኮብል ስቶን ንጣፍ ስራ የተለያዩ ዙር ክፍያዎች ሲፈፀሙ የስራ ስፍር ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 6,826,816.46፣
- አብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈፀሚያ በጀት በጃናሞራ ወረዳ የድልድይ ግንባታ እና በቋራ ወረዳ የገጠር መንገድ ስራ የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈፀም ያለውለታ የተከፈለ ብር 9,343,196.03፣
- ባህር ዳር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል የመንገድ ባለስልጣን ጽ/ቤት በተለያዩ ክፍለ ከተማዎች የኮብል መንገድ/ንጣፍ ስራ ሲሰራ ውለታ ሳይኖረው እና የዘመናዊ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ማምረቻ ሸድ ግንባታ በተለያየ ዙርና የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈጸም ውለታ ሳይኖርና የስራ ስፍር ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ ብር 4,488,043.85፣
- ጎንደር መምህራን ት/ኮሌጅ የአዳራሽ፣ የመማሪያ ክፍል እድሳት እና የአጥር ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም የስራ ስፍር ልኬት ሳይቀርብ የተከፈለ ብር 2,247,048.22፣ ጣቁሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል የወረዳው ንግድና ኢንዱስትሪ ገበያ ልማት ለሚያስገነባው የቢሮ ግንባታ እና የወረዳው ቴክኒክና ሙያ ኢንተርፐራይዞች ልማት መምሪያ ለሚያስገነባው የእንጨት ወርክ ሾፕ ክፍያ ሲፈጽም የስራ ስፍር ወረቀት ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 2,726,597.11፣ ጎንደር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ከተማ ልማት ኮንስትራክሽን መምሪያ ላስገነባው የአዘዞ መናሀሪያ የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈፀም የርክክብ ሰነድ ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ ብር 1,240,559.70፣
- በደቡብ ወሎ ዞን የገንዳ ውሃ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል በተለያዩ ቀበሌዎችና ቀጠናዎች ለተሰራው

የኮብል ስቶን ንጣፍና የውሃ ማፋሰሻ ቦይ ግንባታ የ1ኛ ዙር የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈጸም የስራ ስፍር ልኬት ወረቅት ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 3,857,006.92፣ተሁለደሬ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል የአስተዳደር ጽ/ቤት የቢሮ ግንባታ የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈፀም የስራ ስፍር ወረቀት ሳይቀርብ የተከፈለ ክፍያ ብር 1,916,776.51፣ ደላንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል በቴክኒክና ሙያ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤት በተለያዩ ቀበሌዎች የበግና ዳልጋ ከብት እርባታ ሸድ ግንባታ እና የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት ግንባታ የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈጸም የሥራ ስፍር ወረቀት ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 1,463,525.52 ናቸው፡፡

ስራው ስለመከናወኑ የሚያሳዩ የስራ ልኬት ወረቀት /የክፍያ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት/ ሳይቀርብ እና ርክክብ ሳይፈፀም ክፍያ ተፈፃሞ የተገኘባቸው ሲሆኑ ሥራው በትክክል ስለመሠራቱ በገለልተኛ የምህንድስና ባለሙያ እንዲረጋገጥ ሆኖ ያልተሰራ መሆኑ ከተረጋገጠ ገንዘቡ ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲደረግ እና ድርጊቱን በፈጸሙት ባለሙያዎች ላይ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባዉ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡ የግንባታ ማስረጃ ሳይቀርብ ከተፈጸመው ክፍያ ውስጥ ብር 42,938,340.31 (62%) በባለሙያ የተረጋገጠ ማስረጃ የቀረበለት መሆኑ በግብረ መልስ የተገለጸ ሲሆን ቀሪው ሂሳብ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ይህ ጥንቅር እስከተሠራበት ሰኔ 21/2011 ዓ.ም ድረስ ለመ/ቤታችን አልተገለጸም፡፡

### ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ

37. ማንኛውም ክፍያ ተፈጽሞ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ ሲገባው ይህን በመተላለፍ በ32 (10.84%) መ/ቤቶች የተለያዩ የዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈጸም ለተከፈለው ብር 75,726,827.04 የወጪ ደረሰኝ ወይም ፋክቱር ሳይቀርብለት ክፍያ ተፈጽሞና በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል::

በአጠቃላይ ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ ካለፈው ዓመት ብር 25,281,057.38 ጋር ሲነፃፀር በ2010 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በቁጥር 33 የቀነሰ ሲሆን በገንዘብ መጠን ግን በብር 50,445,767.66 ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ ይህም በማስረጃ አቀራረብ ዙሪያ መ/ቤቶች ከችግሮቻቸው እየተሻሻሉ መምጣታቸውን ቢያመላክትም በአንዳንድ የክልል ቢሮዎች ግን ችግሩ ገዝፎ ታይቷል፡፡ ስለሆነም ክፍያውን የፈፀሙት መ/ቤቶች በከፈሉት ገንዘብ ልክ ተገቢውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ማግኘታቸውን የማያመላክት በመሆኑ ለእያንዳንዱ ክፍያ ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ እንዲያያዝ ወይም ያለማስረጃ የተከፈለው ገንዘብ ከሚመለከተው ላይ ተመላሽ እንዲሆን ለየመ/ቤቶች በፃፍነው ሪፖርት መሠረት ብር 1,489,535.27 ከኦዲት በኋላ ማስረጃ የቀረበለት መሆኑን በሪፖርት ግብረ-መልስ የተገለፀ ሲሆን ቀሪው ብር 74,237,291.77 ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 21/2011 ዓ.ም ድረስ የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ግብረ መልስ አልደረሰም፡፡

**ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ የወጪ ማስረጃዎች፤**

38. ክፍያዎች በተገቢው ማስረጃ ተደግፈውና መ/ቤቱ ለተጠቀመበት ዕቃና አገልግሎት በትክክል ስለመዋላቸው በኦዲት ለማረጋገጥ ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ21 (7.12%) መ/ቤቶች ብር 50,006,652.65 የያዙ የወጪ ማስረጃዎች ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 2,224,237.16(4.4%) ከኦዲት በኋላ ማስረጃ ቀርቦ በውስጥ ኦዲተር የተረጋገጠ መሆኑ በግብረ መልስ ተገልጿል፡፡ ከፍተኛ ወጪ ይዘው ማስረጃ ካላቀረቡት መ/ቤቶች መካከልም ከብር 1,000,000.00 በላይ የያዙ መ/ቤቶች፡-

- ባቲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 15,094,697.08፣ተንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 7,212,727.06፣ ባቲ ከተማ አስ/ ነ/ፋ/ ድ/ስ /ማዕከል ብር 6,717,676.07፣ ወልዲያ ከተማ አስ/ነ/ ፋ/ድ/ ስ/ማዕከል ብር 5,725,396.32፣ሊቦ ከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 3,292,654.22፣ ዳንግላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ ማዕከል ብር 2,025,875.67፣ሳይንት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,503,438.65፣ዋድላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,486,091.25፣ ሃይቅ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 1,476,068.09፣ ኮምቦልቻ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 1,259,428.45፣ አዲአርቃይ ወረዳ ገ/ኢ/ት/ጽ/ቤት ልዩ ኦዲት ብር 1,218,208.36፣

ማስረጃዎቹ ምን እንደተፈፀመባቸውና ለማጭበርበር ድርጊት አለመዋላቸው ባለመረጋገጡ ስጋት ያስከተለ በመሆኑ ቀርበው የወጪው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥ ከማድረግ በተጨማሪ ሰነዶቹን የሰወሩ/ማቅረብ የነበረባቸው ሠራተኞች ተጠያቂ እንዲሆኑ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡ይሁንና በቀሪው ግኝት ላይ ስለተወሰደው እርምጃ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 21/2011 ዓ.ም ድረስ የሚያሳይ ምላሽ ባለመምጣቱ ግኝቱ ያለበትን ሁኔታ ማወቅ አልተቻለም፡፡

**የግዥ ሥርዓትን ያልተከተለ የወጪ ሒሳብ**

39. የዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ አፈፃፀም በስራ ላይ ባለው የዕቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያ መሰረት ስለመፈፀሙ እንዲሁም የተሻለ የዕቃ ጥራትና ዋጋ ለመገኘቱ እና የግዥ አፈፃፀም ሂደቶች የተሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ116 (39.32%) ብር 69,982,706.37 ዋጋ ያላቸው ግዥዎች የግዥ ስርዓት የሚጠይቀውን መስፈርት ሳያሟሉ ተከናውነው ተገኝተዋል፡፡ የግዥ አፈጻፀም ችግሮች ጎልቶ የሚታይባቸው ከብር 1,200,000.00 በላይ የገንዘብ መጠን ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች፡-

- **ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ብር 8,985,703.63** ለተሽከርካሪ መለዋወጫ ግዥ ሲፈጸም አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በቀጥታ ግዥ ዘዴ የተፈጸመ ግዥ እና በቢሮው እና በአማራ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት መካከል የህንፃ ግንባታ ስራ ሲፈጸም የውል ስምምነቱ በፍትህ አካላት ተመርምሮ ከመጽደቁ በፊት ለተቋራጩ ቅድሚያ ክፍያ ተከፍሎ የተገኘ፣
- **አብክመ ፖሊስ ማሰልጠኛ ኮሌጅ ብር 4,331,917.68** ለሰልጣኝ ፖሊሶች የምግብ ግብዓት ግዥ ሲከናወን፣ የፕሮጀክተር ግዥ፣አልባሳት ግዥ፣የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች ግዥ ሲፈጸም ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር ህጋዊ የውል ስምምነት ሳይያዝ የተፈፀመ ግዥ፣
- **ቀወት ወረዳ /ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 2,763,522.98** ገ/ኢ/ትብብር ጽ/ቤት የፈርኒቸር፣የመኪና ጎማ ግዥ ሲገዛ በግልጽ ጨረታ መገዛት ሲገባ በውስን ጨረታ የተገዛ፣ግብርና ጽ/ቤት፣ውሃ ሀብት ልማት ጽ/ቤት እና ቴ/ክ/ሙ/ል/ጽ/ቤት የስሚንቶ ግዥ ሲፈፀም ከግዥ በፊት የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለ፣
- **አለም ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 2,380,895.22** ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት ለሚያሠራው የውስጥ ለውስጥ መንገድ በቀጥታ የተገዛ የተረጋ ስራ እና በአካባቢ ማስታወቂያ የተገዛ የስሚንቶ ግዥ ፣የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት የትራክተር ግዥ፣ ለተለያዩ ሴክተር ጽ/ቤቶች የጽህፈት መሳሪያ ግዥ ሲፈፀም ከግዥ በፊት የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት፣
- **መርጦለማሪያም ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ልዩ ኦዲት ብር 2,335,809.16** አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በ2007 በጀት ዓመት በቀጥታ ግዥ የተፈፀመ እና በውስን ጨረታ የተፈፀመ ጽ/መሳሪያ ግዥ ብር 1,590,562.05፣ አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በ2008 በጀት ዓመት በውስን ጨረታ የተፈፀመ የመፀዳጃ ቤት ግንባታ፣አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በ2009 በጀት ዓመት በውስን ጨረታ የተፈፀመ ጽ/መሳሪያ ግዥ፣በ2010 በጀት ዓመት የጽ/መሳሪያ ግዥ ሲፈፀም አንድ አቅራቢ ብቻ በተሳተፈበት የግልጽ ጨረታ ሂደት የተፈፀመ ግዥ፣
- **ጉባላፍቶ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 2,166,160.21** ገጠር መንገድ ጽ/ቤት ሸማ ፈጅና ቆላይት ቀበሌ ላሠራው መንገድ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ግዥ፣ገ/ኢ/ል/ትብብር /ጽ/ቤት የጽህፈት መሳሪያዎችና ቋሚ ዕቃ፣ኤሌክትሮኒክስ ግዥ ያለ በቂ ምክንያት በውስን ጨረታ የተገዛ፣ የአስተዳደር ም/ቤት ሞባይል ካርድ ግዥ ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ የሚያሳይ የንብረት ደረሰኝ ሳይቀርብ የተገኘ፣
- **አምባሰል ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 2,046,502.03 የግብርና ጽ/ቤት ዶዘር ኪራይ ያለአሳማኝ ምክንያት በውስን ጨረታ የተገዛ፣ ውሃ ሃብት ልማት ጽ/ቤት በ08 እና 09 ቀበሌ የመጠጥ ውሃ መስመር ዝርጋታ ያለአሳማኝ ምክንያት በፕሮፎርማ የግዥ ዘዴ የተገዛ እንዲሁም ያለአሳማኝ ምክንያት በውስን ጨረታ የተገዛ የግንባታ ግብዓቶች ግዥ ፣መንገድ ትራንስፖርት ጽ/ቤት በ03 ቀበሌ ለተሠራው መንገድ ጥገና የዶዘር ኪራይ ሲፈፀም ያለአሳማኝ ምክንያት በውስን ጨረታ የተገዛ፣በሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት ያለአሳማኝ ምክንያት በፕሮፎርማ የተገዛ የደንብ ልብስ ግዥ፣በመሬት አስ/አጠ/ጽ/ቤት ያለአሳማኝ ምክንያት በፕሮፎርማ የተገዛ የቢሮ ዕቃ ግዥ ፣

- **ገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ብር 1,546,617.87** ለአጅባር መንገድ ስራ ፕሮጀክት ቋሚ እቃዎች እና ለወገል ጤና መንገድ ስራ ፕሮጀክት ለዶዘር መለዋወጫ ዕቃ ግዥ ሲፈፀም በግልጽ ጨረታ መፈጸም ሲገባው አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በፕሩፎርማ የግዥ ዘዴ የተፈፀመ ግዥ፣ የተሽከርካሪ ጥገና ሲከናወን አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በቀጥታ የግዥ ዘዴ የተፈጸመ ጥገና፣ለጎጃም ገጠር መንገድ ጥገና ጽ/ቤት ተሽከርካሪዎች መለዋወጫ ግዥ ሲፈፀም አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በቀጥታ ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ፣
- **አርጡማ ፋርሲ ወረዳ /ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 1,449,499.47** የግብርና ጽ/ቤት መኪና ሲጠገን ያለአሳማኝ ምክንያት በቀጥታ የተገዛ ፣ጋቢዎን ሲገዛ ያለአሳማኝ ምክንያት በፕሮፎርማ ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ የተገዛ እና ከግዥ በፊት የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት፣
- **ለጋምቦ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር** 1,371,107.12 ለተለያዩ ሴክተር ጽ/ቤቶች ኮምፒተር ሲገዛ ያለአሳማኝ ምክንያት በውስን ጨረታ የተገዛ፣መኪና ጥገና መለዋወጫ ዕቃ ግዥ ሲፈጸም ያለ አሳማኝ ምክንያት በውስን ጨረታ የተገዛ፣ የመኪና ጎማ ግዥ ሲፈጸም ያለ አሳማኝ ምክንያት በውስን ጨረታ የተገዛ፣ የኮምፒተር ግዥ ከግዥ በፊት የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለ፣ ለጤና ጣቢያዎች አገልግሎት የሚውል የመድሃኒት ግዥ የግዥ ጥያቄ ሳይቀርብ የተገዛ፣
- **ሊቦ ከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,273,958.38** የወረዳው አስተዳዳር ጽ/ቤት በሚያስገነባው አዳራሽ እና የመጸዳጃ ቤት ግንባታ፣የመኪና ጎማ፣ቆርቆሮ እና ሚስማር ግዥ ሲከናወን በግልጽ ጨረታ መከናወን ሲገባው አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በውስን ጨረታ የተከናወነ ግዥ፣
- **ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,227,676.54** የደብረ ብርሃን ቅርንጫፍ ስነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን የቢሮ ኪራይ ግዥ ያለአሳማኝ ምክንያት በቀጥታ ግዥ የተገዛ፣ግብርና ጽ/ቤት የማንጎ ዘር ግዥ ከግዥ በፊት የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት፣ሞባይል ካርድ ተጠቃሚ ለሆኑ ጽ/ቤቶች ሞባይል ካርድ ግዥ ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ የሚያሳይ የንብረት ደረሰኝ ሳይቀርብ የተገኘ፣
- **መቅደላ ወ/ነ/ፋ/ድ/ማዕከል** ብር 1,206,966.25 ለቴ/ሙ/ኢ/ጽ/ቤት ለግንባታ የሚውሉ የፋብሪካ ውጤቶች ግዥ በውስን ጨረታ የተገዛ፣ ገ/ኢ/ትብብር ጽ/ቤት የፍራሽ ግዥ ሲፈፀም ህጋዊ ፈቃድ ከሌለው የተገዛ፣ ግብርና ጽ/ቤት የሞተር ዘይት ግዥ የፈፀመበት ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ የሚያሳይ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተገኘ፣መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ግኝቱ ሊከሰት የቻለውም የግዥ ህጉን በተገቢው መንገድ በሥራ ላይ ካለማዋል የተነሣ ገንዘቡ ተገቢዉን ዕቃ (አገልግሎት) ሳያስገኝ እና ፍትሃዊ ውድድርን ሳያስተናግድ ግዥ እየተፈፀመ እንደሆነ በማስገንዘብ ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በኦዲት ሪፖርቶች አሣስበናል፡፡

የ2010 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገዉ የግዥ ሂሳብ ከ2009 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝት

ብር 119,427,957.14 ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት ቁጥር በ24 እና በገንዘብ መጠን በብር 49,445,250.77 ቀንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የግዥ መመሪያውን በመከተል በኩል አፈፃፀማቸው የተሻለ እንደነበር ያመላክታል፡፡

**የተከፋይ ሂሳብን በተመለከተ፤**

**በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ፤**

40. የ2010 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ85 መ/ቤቶች ብር 652,805,367.12 ተከፋይ ዕዳ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ወቅት የፋይናንስ መመሪያውን ተከትሎ ሳይከፈል ተገኝቷል።

በወቅቱ ያልተከፈለ ወይም ወደ ተጣራ ሀብት መቀየር ያለበት ተከፋይ ሂሳብ ካለፈው ዓመት ብር 1,129,063,839.25 ጋር ሲነፃፀር በ2010 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የተገኘው በመ/ቤቶች ቁጥር በ27 እና በገንዘብ መጠን በብር 476,258,472.13 ቀንሶ ተገኝቷል። ይህም በወቅቱ ያልተከፈለ ዕዳ ክምችት ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች እየቀነሰ መሄዱን ያመለክታል። በወቅቱ ያልተከፈለ ከብር 20 ሚሊዮን በላይ ከፍተኛ የተከፋይ ሂሳብ ከሚታይባቸው መ/ቤቶች መካከል፡-

- ኮምቦልቻ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 77,318,700.72፣ ጎንደር ከተማ አስ/ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 73,245,680.30፣ ደብረ ብርሃን ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 44,916,736.75፣ ዋግኽምራ ብሄረሰብ ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 40,786,233.89፣ሰሜን ወሎ ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 29,381,418.09፣ የአብክመ ስራ-አመራር አካዳሚ ብር 26,085,349.63፣ ፎገራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ ማዕከል ብር 24,813,878.78 ከፍተኛውን ድርሻ ይሸፍናሉ፡፡

ተከፋይ ሂሳቦች የራሳቸው የተወሰነ የመክፈያ ወይም ወደ ተጣራ ሀብት የሚቀየሩበት ጊዜ ስላላቸው በመመሪያው መሠረት ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ባሳሰብነው መሰረት ስለተወሰደው እርምጃ በተሰጠው ምላሽ ብር 46,533,429.10 (7%) ከኦዲት በኋላ ለባለጥቅሙ የተከፈለ ወይም ተገቢው እርምጃ የተወሰደበት መሆኑ የተገለፀ ሲሆን ቀሪው ብር 606,271,938.02 ስለተወሰደው እርምጃ ባለመገለጹ ይህ ዘገባ ጥንቅር እስከተሰራበት ሰኔ 21/2011ዓ.ም ድረስ ተከፋይ ሂሳቡ ስላለበት ደረጃ የታወቀ ሁኔታ የለም፡

**ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት ተከፋይ ሂሳብ፣**

41. በወቅቱ ካልተከፈለው የተከፋይ ሂሳብ ላይ በ32 መ/ቤቶች ብር 50,554,737.24 በመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለማን እንደሚከፈልና መቸ እንደሚከፈል የሚያሳይ ዝርዝር የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል።

ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለትን ተከፋይ ሂሣብ በተመለከተ በጥቅሉ ስለተመዘገበ ገንዘቡ ለማንና መቸ

እንደሚከፈል ገላጭ ባለመሆኑ በሥራ ላይ ያለውን የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት በመከተል በየጊዜው ክትትል እየተደረገ በየባለቤቱ ተለይቶ መመዝገብ ወይም ለሚመለከተው መከፈል ካልቻለም ወደ ተጣራ ሀብት መቀየር እንዳለበት በሪፖርታችን ብናስገነዝብም ከዚህ ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ሰኔ 21/2011 ዓ.ም ድረስ ከደረሰን ግብረ መልስ እንደተረጋገጠው ለምን ያህሉ የተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀር የተዘጋጀ ስለመሆኑ ማወቅ አልተቻለም፡፡

## የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ኦዲት ውጤት

42. የመንግስት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 አንቀጽ 53 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 02/2003 እና ተያያዥ የህግ ማዕቀፎች አግባብ ንብረቶች በአግባቡ ተመዝግበው፣ክትትል እየተደረገባቸውና በየዓመቱ ቆጠራ እየተከናወነ የንብረት ሒሳቡም በመ/ቤታችን ኦዲት መደረግ ይኖርበታል፡፡ በዚሁ መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 235 መ/ቤቶች መካከል በ112(47.7%) መ/ቤቶች የንብረት ኦዲት ማድረግ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ በመሆኑም የተጠቀሱትን የንብረት አስተዳደር ግድፈቶች በማረም የመንግስት ሃብት ብክነት እንዳይከሰት ተገቢው የንብረት አስተዳደር፣ አያያዝና አጠቃቀም በየመ/ቤቱ እንዲጠናከር በየሪፖርቶቻችን አሳስበናል፡፡

## የንብረት ሂሳብ ጉድለት

43. የ2010 በጀት ዓመት ሂሣባቸው በልዩ ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች በድምሩ ብር 148,463.18 ጉድለትና ማጭበርበር የተገኘ ሲሆን ጉድለት/ማጭበርበር የተገኘባቸው መ/ቤቶች ዝርዝር፡-

- ዳንግላ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 120,932.00 አንድ ባለሙያ የከተማውን የመንገድ ዳር መብራት አምፑል ለመግጠም ከንብረት ክፍል ወጭ አድርገው አምፑል እና ፊክቸር ከነሙሉ አክሰሰሪው የወሰዱ ሲሆን ይህው ንብረት ለስራ መዋሉ ኦዲት ሲደረግ በጉድለት የተገኘ እና በጥንቃቄ ማነስ ምክንያት ለብልሽት የተዳረገ የመንግስት ንብረት፣
- መንታ ውሃ 1ኛ ደ/ት/ቤት ብር 26,892.01 የንብረት ክፍል ሰራተኛ ያንቀሳቀሱት የንብረት ሂሳብ ሲመረመር የተገኘ ጉድለት፣
- የሸበል በረንታ ወረዳ የሞኾሮን 1ኛ ደ/ት/ቤት ብር 639.17 የትምህርት ቤቱ ንብረት ክፍል ሰራተኛ የነበሩት ያንቀሳቀሱት የንብረት ሂሳብ ሲመረመር የተገኘ ጉድለት፣

በመሆኑም ከንብረት ሰራተኞች የሚፈለገው ጉድለት ላይ ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካከትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ብናሳስብም በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በምላሹ አልተገለፀልንም፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባዔ!**

**የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

**ያለፉት ዓመታት የኦዲት ውጤቶች እርምጃ አወሳሰድ የክትትል ኦዲት ሪፖርት**

የ2010 በጀት ዓመት ሂሳባቸው በመ/ቤታችን መደበኛ ኦዲት በተደረጉ 235 መ/ቤቶች በተደረገው የክትትል ኦዲት በ2009 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ተደርገው በተገኙ ግኝቶች ላይ በተቋማት ያለው የማሻሻያ እርምት እርምጃ አወሳሰድ ሲጣራ በ20 መ/ቤቶች በተሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት ይህ የጥንቅር ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ቀን ሰኔ 21/2011 ዓ.ም ድረስ የእርምት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ያለፈው ዓመት የኦዲት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡ በተለይም፤

- **አላግባብ/በብልጫ/ ላልተሰራ** ስራ የተከፈሉ ውሎ አበል እና ሌሎች ክፍያዎች በድምሩ ብር 4,261,404.98 ከሚመለከታቸው አካላት ላይ መተካት ሲገባው ይህ አለመፈፀሙ የተጠያቂነት አሰራሩ የላላ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ጉዳዩን መከታተል እና የእርምት እርምጃ መውሰድ የሚገባቸው አካላት በህግ ሊጠየቁ እንደሚገባና በቀጣይም እርምጃ መወሰድ እንደሚያስፈልግ በድጋሜ ሪፖርት አድርገናል፡፡
- **ለኦዲት ስራ ሳይቀርቡ** እና በውስጥ ኦዲተር ሳይረጋገጡ የቀሩ ገቢ የተሰበሰበባቸው የገቢ ማስረጃዎች ብር 2,931,846.43 እና ወጭ የተፈፀመባቸው የወጭ ማስረጃዎች ብር 6,596,179.38 ላይ የእርምት እርምጃ ሳይወሰድ መገኘቱ፤

የሚያስጠይቅና ተግባሩም ለሌሎች ተቋማትም መልካም ያልሆነ ተግባር ሆኖ የሚታይ ከመሆኑም በላይ በማስረጃዎቹ ምን እንደተፈፀመ ባለመታወቁ ከፍተኛ ስጋት ያሳደረ በመሆኑ በአስተያየቱ መሠረት ተገቢ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ በነበረባቸው አካላት ላይ አስፈላጊው ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድና በቀጣም ትኩረት ሊደረግ ይገባል በሚል በሪፖርት አሳስበናል፡፡ ዝርዝሩ ከዚህ ቀጥሎ በየመ/ቤቶች ተለይቶ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- **አሳግርት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** በውለታው መሰረት ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ ብር 20,091.06፣በብልጫ የተከፈለ ወጭ ብር 141,684.73፣ ገንዘቡን ለመቀበሉ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 124,676.28፣ህጋዊ ባልሆነ ደረሰኝ የተከፈለ ሂሳብ ብር 81,799.80፣ላልተሠራ ሥራ የተከፈለ ሂሳብ ብር 32,000.00 ፣አለአግባብ የተከፈለ የማሽን ኪራይና የስልጠና ወጪ ብር 46,222.05፣አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 16,769.20፣
- **አርጎባ ብሄረሰብ ልዩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት ግዥ ብር 164,681.68፤ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 1,273,430.00፣ ከመንግስት በጀት ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ ብር 41,119.86 እና አላግባብ የተከፈለ የውሎ አበልና የነዳጅ ሂሳብ ብር 36,953.94፣
- **ለገሂዳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 17,994.44፣ በውለታው መሰረት ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ ብር 23,166.76 እና ለኦዲት ስራ ያልቀረበ የወጪ ሠነድ ብር 58,526.00፣

- **ሰቆጣ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ያለይዞታ ማረጋገጫ የተከፈለ የመሬት ካሳ ወጪ ብር 1,767,680.00 እና ላልተሠራ ሥራ የተከፈለ የካፒታል ወጪ ብር 1,896,962.92፣
- **ባቲ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** በብልጫ የተከፈለ ወጪ ብር 34,748.37፣ለኦዲት ሥራ ያልቀረበ የወጪ ሠነድ ብር 6,537,653.38፣
- **ሊቦ ከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ለኦዲት ሥራ ያልቀረበ የስፖርት ም/ቤት ገቢ ደረሰኝ ብር 36,380.00 እና በውሉ መሰረት ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ ብር 20,338.65፣
- **ፎገራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ለኦዲት ሥራ ያልቀረበ የስፖርት ም/ቤት እና የመደበኛ ገቢ ደረሰኝ ሂሳብ ብር 31,620.00 እና ያለ ማስረጃ በወጪ የፀደቀ ሂሳብ ብር 159,468.00፣
- **ቆቦ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 42,966.60፣
- **ላሊበላ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** በውሉ መሰረት ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ ብር 624,718.29፣
- **ደላንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ለመቀበሉ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 100,000.00፣
- **ቀወት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** በብልጫ የተከፈለ ሂሳብ ብር 13,124.04 እና አላግባብ የተከፈለ ውሎ ውሎ አበል ብር 25,862.98፣
- **ጣርማ በር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** አላግባብ የተፈፀመ የዶዘር ኪራይ ወጭ ብር 84,223.12፣
- **ሲያ ደብርና ዋዩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ለመቀበሉ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 11,377.00፣
- **ከሚሴ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ለኦዲት ሥራ ያልቀረበ የመደበኛ ገቢ ደረሰኝ ብር 2,677,276.43፣
- **ደዋ ጨፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ለኦዲት ሥራ ያልቀረበ የስፖርት ም/ቤት ገቢ ደረሰኝ ብር 186,570.00 እና አላግባብ የተከፈለ የውሃ ግንባታ ሂሳብ ብር 10,000.00፣
- **ገንዳ ውሃ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** የሥራ ስፍር ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ የተከፈለ የግንባታ ክፍያ ብር 58,707.51፣
- **መካነ ሰላም ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበልና በብልጫ የተከፈለ ሂሳብ ብር 19,302.15፣
- **አዲስ ዘመን ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** የሥራ ስፍር ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ የተከፈለ የግንባታ ክፍያ ብር 12,261.60፣
- **ደጀን ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ያልተቀነሰ የንግድ ስራ ትርፍ ግብርብር 10,342.39፣
- **አብክመ ክልል ም/ቤት** ያለአግባብ ለግለሰብ ህክምና የተከፈለ ድጋፍ ብር 10,000.00፣

እነዚህ በእያንዳንዱ የግኝት እርዕስ ከብር 10,000.00 በላይ የሆኑ በ20 መ/ቤቶች የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ግኝቶች በወቅቱ በተሰጠው የኦዲት ማሻሻያ አስተያየት መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሜ እያሳሰብን የፋይናንስ ግልጽ አሰራርና ተጠያቂነት እንዲጠናከር መ/ቤታችን ከሚመለከታቸው የፍትህ አካላት ጋር በትብብር የሚሰራውን ተግባር አጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን የእርምት እርምጃ በማይወስዱ እንዲሁም ምላሽ በማይሰጡ አካላት ላይ በህግ አግባብ እንዲጠየቁ የሚሰራ ይሆናል፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባዔ!**

**የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

**የማጠቃለያና የማሻሻያ አስተያየቶችን ከዚህ ቀጥሎ አቀርባለሁ፡፡**

**የኦዲት አስተያየትን በሚመለከት፤**

44. የ2010 በጀት ዓመት ሒሳባቸው በመደበኛነት ኦዲት ከተደረጉ 235 መ/ቤቶች ውስጥ ለ25 (8%) ***"ንፁህ"*** የሚል የኦዲት አስተያየት እንዲሁም 204 (69%) **" ከዚህ በስተቀር"** የሚል ኦዲት አስተያየት ያገኙና **‹‹አስተያየት መስጠት አልተቻለም››** እና **‹‹አጥጋሚ አይደለም››** የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው መ/ቤቶች ብዛት ውስን መሆኑ አብዛኞቹ የክልላችን መ/ቤቶች የክልሉን የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት አድረገው በጀትን ለመምራት ጥረት እያደረጉ መሆኑን ያመላክታል፡፡

**ምላሽ አሰጣጥን በሚመለከት**

45. የ2010 በጀት ዓመት ሒሳባቸው ኦዲት የተደረጉ ተቋማት በምላሽ አሰጣጥ ረገድ እየተሸሻሉ የመጡ ቢሆንም አሁንም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ በኩል እጥረቶች እንዳሉባቸው ያሳያል፡፡

**የጥሬ ገንዘብ ሒሳብ ኦዲትን በሚመለከት**

46. የ2010 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች በድምሩ ብር 3,321,989.12 ጉድለት የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የተተካው ብር 200,811.99 (6%) መሆኑ ጉድለትን የማስተካከት ሂደቱ አዝጋሚ እርምጃ መሆኑን ያሳያል፡፡ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ መከታተያ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበት እና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲነጻጸር በ10 መ/ቤት ብር 3,712,513.03 የቆጠራ ውጤት ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በማነስ መገኘቱ እና በ1 መ/ቤት ቆጠራ ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በመብለጥ ብር 47,196.51 ሆኖ መገኘቱ በጥሬ ገንዘብ አያያዝና ቁጥጥር ስርዓቱ ትግበራ ላይ መላላትና የአሰራር ክፍተት መኖሩን የሚያሳይ ሲሆን ለኦዲት ምቹ ቅድመ ሁኔታዎች ባለመሟላታቸው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2010 ዓ.ም ላይ በ56 መ/ቤቶች ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች ናቸው፡፡

**የገቢ ሂሣብን በተመለከተ**

47. የ2010 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መካከል በ2 መ/ቤቶች ብር 1,455,423.90 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም የ□ለ፤በ2 መ/ቤቶች ብር 263,430.21

የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብለት ክፍያ ተፈጽሞ የተጨማሪ እሴት ታክሱ ለመንግስት ገቢ ሳይሆን የተገኘ ሲሆን በ89 መ/ቤቶች ብር 154,154,046.04 ሥራ ላይ ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት በወቅቱ ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡በ4 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 179,536.21 ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ መሰሠብሰብ የሚገባው የንግድ ስራ ትርፍ ግብር ሳይሰበሰብ ተገኝቷል እንዲሁም ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሟልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ21(7.12%) መ/ቤቶች ብር 94,077,151.66 የያዙ የገቢ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሲሆን ይህም በገቢ ሂሳብ አሰባሰብና አያያዝ ውስንነትመኖሩን ያመለክታል፡፡

**ተሰብሳቢ ሂሳብን በሚመለከት**

48. የ2010 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ92 መ/ቤቶች ብር 865,021,013.48 በወቅቱ በፋይናንስ የአሠራር ስርዓት መሠረት ሣይሰበሰብ (ሳይወገድ) ተገኝቷል፡፡ በ4 መ/ቤቶች የ3ተኛ ወገን ማረጋገጫ ያልቀረበለት ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 11,160,917.53 መገኘቱ፣በ1 መ/ቤት ብር 188,488.43 ትክክለኛ ተሰብሳቢ ሂሳብ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ሠነድ፣መቸ እንደተሰጠ፣ከማን እንደሚሰበሰብ እና ለምን እንደተሰጠ ምንጩ ሳይታወቅ በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ መገኘቱ እና በ14 መ/ቤቶች ብር 187,513,514.93 የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመተላለፍ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡ ይህም የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት በተገቢ ማስረጃ አለመደገፍና በወቅቱ አለመሰብሰብ ውሎ አድሮ ያለመሰብሰብ እድልን የሚያሰፋ መሆኑን ያመለክታል፡፡

**የወጪ ሂሳብን በሚመለከት**

49. በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መካከል በ10 መ/ቤቶች ብር 26,537,407.04 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ መገኘቱ ሲሆን በ11 መ/ቤቶች ለስራ ተቋራጮች የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 3,027,011.70 በትክክል ለሚመለከተዉ ገቢ ሠብሳቢ መ/ቤት ፈሠስ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብለት ተገኝቷል፡፡ ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ሲጣራ በ77(26%) መ/ቤቶች የተለያየ ዕቃና አገልግሎት የተፈጸሙ ክፍያዎች በድምሩ ብር 7,869,866.10 አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው ይህ ባለመደረጉ በ43(14.6%) መ/ቤቶች በድምሩ ብር 69,136,212.19 ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፤

በ32 (10.84%) መ/ቤቶች የዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈጸም ለተከፈለው ብር 75,726,827.04 የወጪ ደረሰኝ /ፋክቱር ሳይቀርብለት ክፍያ ተፈጽሞና ተመዝግቦ መገኘቱ፤ክፍያዎች የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ21(7.12%) መ/ቤቶች ብር

50,006,652.65 የያዘ የክፍያ ማስረጃ ለኦዲት ሳይቀርብ መቅረቱ፤ በ116 (39.32%) መ/ቤቶች ብር 69,982,703.37 ዋጋ ያላቸው የእቃና የአገልግሎት ግዥዎች የግዥ ስርዓትን የሚጠይቀውን መስፈርት ሳያሟሉ ተከናውነው ተገኝተዋል፡፡

## የተከፋይ ሂሳብን በሚመለከት

50. የ2010 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረገት መ/ቤቶች መካከል በ85 መ/ቤቶች ብር 652,805,367.12 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሠረት ያልተከፈለ ወይም ወደ ተጠራ ሀብት ያልተቀየረ ተከፋይ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥም በ32 መ/ቤቶች ብር 50,554,737.24 በመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለማን እንደሚከፈልና መቼ እንደሚከፈል የሚያሳይ የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡

## የንብረት አያያዝ፤ አጠባበቅና አጠቃቀምን በተመለከተ

51. የ2010 በጀት ዓመት ሒሣባቸው በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 235 መ/ቤቶች መካከል በ112(47.7%) መ/ቤቶች የንብረት ኦዲት ማድረግ ሳይቻል የቀረ ሲሆን ኦዲት ከተደረጉ ሌሎች መ/ቤቶች ብር 148,463.18 በጉድለትና በማጭበርበር ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባዔ!**

**የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

**ከዚህ ቀጥሎ የማሻሻያ አስተያየቶችን አቀርባለሁ፡፡**

በዚህ በጀት ዓመት ባቀረብነው የመ/ቤታችን ዕቅድ አፈፃጸም ላይ የተስተዋሉ ውስንነቶች፣ በኦዲት ተደራጊዎች የታዩ ግኝቶች ተሻሽለው የኦዲት ሽፋናችን እንዲያድግና የመንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስና የንብረት አስተዳደር አመራር ሥርዓት መጠናከር እንዲችል የሚከተሉትን የማሻሻያ አስተያየቶች አቀርባለሁ፡፡

**የኦዲት ሽፋንን ለማሳደግ ጥራቱን እና ወቅታዊነቱን የጠበቀ ለማድረግ ከአደረጃጀት አንጻር ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡**

52. በክልላችን ያለው ልማት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጐለበት በመምጣቱ የኦዲት ተደራጊ ተቋማት ብዛትና በጀት እየጨመረ የሚገኝ በመሆኑ የኦዲት ሽፋንኑን ማሳደግን አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም ጥራቱንና ወቅታዊነቱን የጠበቀ ሪፖርት ማቅረብ ወሳኝ ነው፡፡

    ከዚህ ጋር በተያያዘ በተለይም ማህበረሰቡ ስለ ኦዲት ሙያ ግንዛቤ በመያዙና የጥቆማ ተሳትፎው በመጨመሩ እንዲሁም ለፍትሃዊ የውሳኔ አሰጣጥ ሲባል በየደረጃው ካሉ ፍርድ ቤቶችና የስነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን የሚቀርቡ የልዩ ኦዲት ጥያቄዎች በስፋት እየቀረቡና በተለየ ትኩረት ተይዘው ካልተሰሩ አሁን ባለው አደረጃጀት ከመደበኛው ኦዲት ስራ ጋር ደርቦ በመስራት ለጥያቄው ወቅታዊ ምላሽ ለመስጠት ያላስቻለና ከስራው ጥራትና ብዛት አንጻር ራሱን በተለየ አደረጃጀት መምራት አስፈላጊ አድርጎታል፡፡

    ይኸውም የልዩ ኦዲት ስራ ከባህሪው፣ ካስቸኳይነቱና በህግ ፊት ለቀጠሮ የሚፈለግ መሆኑ፣ ከዓመት ዓመት በስፋት እየጨመረ በመምጣቱና ጊዜ የማይሰጠው ስራ በመሆኑ የመደበኛ ስራውን ሊያስቆም በሚችል ደረጃ ጫና እያስከተለ በመምጣቱ ራሱን በቻለ ዳይሬክቶሬት መምራት ይቻል ዘንድ አደረጃጀቱ ምላሽ እንዲያገኝ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

**የኦዲት ግኝቶች እርምጃ አወሳሰድና ማሻሻያ አስተያየቶች ትግበራ ሊጠናከር ይገባዋል፡፡**

53. ኦዲት ተደራጊዎች በምላሽ አሰጣጣቸው እየወሰዱት ያለው እርምጃ በቂ ሆኖ ባለመገኘቱ መልስ በማይሰጡና እርምጃ በማይወስዱ፣ በኦዲት አገልግሎቱ እየተጠቀሙ ከዓመት ዓመት በማይሻሻሉ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ላይ በየደረጃው በሚገኙ የምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎችና የፍትህ አካላት አማካኝነት ክትትል ሊደረግበት እንዲሁም የኦዲት እርምጃ አወሳሰድ ክትትልና ድጋፍ ግብረ ኃይል በየደረጃው በማቋቋምና በማጠናከር የግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓቱ ሊጠናከር ይገባል፡፡

ይህን ክትትልና ተጠያቂነት ለማጠናከር በመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዩች ቋሚ ኮሜቴ (Public Accounts Committee) በክልሉ ምክር ቤት መቋቋም ይችል ዘንድ ከፌደራልና ከሌሎች አቻ ክልሎች የተወሰደው ልምድ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**የቋሚና አላቂ ዕቃዎች አያያዝና አጠባበቅ መጠናከር የሚገባው ነው፡፡**

54. በአብዛኞቹ መ/ቤቶች የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ ተቋቁሞ የማይሠራባቸውና በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ቆጠራ የማይከናወን በመሆኑ የንብረት አያያዝና አጠባበቅን ኦዲት አድርጐ አስተያየት መስጠት ያልተቻለ ስለሆነ መ/ቤቶቹ ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ በማቋቋምና በየጊዜው ቆጠራ እያከናወኑ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪው ጋር እያገናዘቡ ልዩነት ሲፈጠርም ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እየወሰዱ ሊሰሩ ይገባል፡፡

በመጨረሻም የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፣ የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤዎች፣ የበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች፣ የፍትህ አካላትና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሥራ ሂደት ላደረጋችሁልን የስራ ትብብር እና የመ/ቤቱ ሠራተኞች ደግሞ በዚህ ሪፖርት ለተገኙትና ሌሎች ውጤቶች ላሳያችሁት ታታሪነትና የሙያ ስነ-ምግባር ከፍተኛ ምስጋና እያቀርብኩ ሪፖርቴን በዚሁ አጠቃልላለሁ፡፡ አመሰግናለሁ!!

ገረመው ወርቁ ካሴ (ረዳት ፕሮፌሰር)

ዋና ኦዲተር

ሰኔ/2011 ዓ.ም

ባህር ዳር!!